# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 128 ጥር 8 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


## «ኢትዮጵያ በቀጣናው ላይ የምታደርገውን አስተዋጽኦ የሚመጥን ጥቅም ልታገኝ ይገባል»

- ፍጹም አረጋ
በካናዳ የኢትዮጵያ አምባሳደር


ፎቶ ፡ ዳኜ አበራ

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ላይ የምታደርገውን በጎ አስተዋጽኦ የሚመጥን ተጠቃሚነት ሊኖራት ይገባል ሲሉ በካናዳ የኢትዮጵያ አምባሳደር ፍጹም አረጋ ገለጹ።

አምባሳደር ፍጹም ኢትዮጵያ የባህር በር የምታገኝበት የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ከሶማሊላንድ ጋር መፈራረሟ ለሀገሪቷ ብሎም ለቀጣናው ያለውን ፋይዳ አስመልክተው ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ ኢትዮጵያ የባህር በር ብታገኝ ፈጣን የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስኬድ ፤ በባህር በኩል ያላትን የገቢና ወጪ ንግድ እንቅስቃሴዋን ለማሳለጥ፤ ሊመጣ የሚችለውን የደህንነት ስጋትንም በባህር ሃይል አማካኝነት በማስከበር ረገድ የሚኖራት ሚና ትልቅ ይሆናል ብለዋል። ስለዚህም ሀገሪቷ በአፍሪካ ቀንድ እየከፈለች ያለውን መስዋዕትነት የሚመጥን ተጠቃሚነት ልታገኝ እንደሚገባ ገልጸዋል።

ስምምነቱ ኢትዮጵያንና ሶማሊላንድን የተሻለ ተጠቃሚ ከማድረግ አልፎ፤ አካባቢው ላይ የኢኮኖሚ ትስስር በመፍጠር የጋራ ተጠቃሚ መሆን የሚቻልበትን መንገድ የሚያጠናክር እንደሆነ አምባሳደር ፍጹም ተናግረዋል።

እንደ አምባሳደር ፍጹም ገለጻ፣ በአካባቢው ላይ ኢትዮጵያ በአሚሶምም ሆነ በራሷ በኩል ባደረገቻቸው የሠላም ማስከበር ሂደቶች የአልሸባብን ስጋት ለመቋቋም ሶማሊያ ውስጥ በርካታ መስዋዕትነት ስትከፍል ቆይታለች። በተከፈሉ መስዋዕትነቶች ሠላም ማምጣት ተችሏል። የሶማሊያ

«ኢትዮጵያ በቀጣናው... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## ትርክቶች የፈተኑት አብሮነት

ተስፋ ፈሩ

ዜና ትንታኔ

ኢትዮጵያ የተለያየ ማንነት፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖትና ልማድ ያለው ሕዝብ በአንድነት የሚኖርባት ሀገር ናት። ሕዝቧ ለረጅም ጊዜ በዘለቀ የአብሮነት ጉዞ በአንድነት በመቆም ደማቅ ታሪኮችን ጽፏል። በብዙ መንገድ እርስ በእርሱ የተሳሰረው ይህ ድንቅ ሕዝብ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አብሮነቱን የሚፈትኑ አጋጣሚዎችን እየተጋፈጠ ነው። ይህ ለምን ሊፈጠር ቻለ? ደማቅ ኢትዮጵያዊ እሴት የሆነውን "አብሮነት" እያጋጠመው ካለው ፈተና ታድጎ ጠብቆ ለማቆየትና ለቀጣዩ ትውልድ ለማቀበል ምን መደረግ አለበት?


መጋቢ ምስጢር አእመረ


ኡስታዝ አቡበከር አህመድ


ፓስተር ፃዲቁ አብዶ

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር ማስተርስ ዲግሪያቸውን ያገኙት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ መምህሩ መጋቢ ምስጢር አእመረ ፀሐዩ፤ ኢትዮጵያ ከሦስት ሺ ዘመናት በላይ ሃይማኖተኛ ሕዝቦችን

ትርክቶች... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



## ክልሉ በተፈጥሮ ማዳበሪያ 7 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር ለማልማት አቅዷል

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- በተፈጥሮ ማዳበሪያ ሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት ማቀዱን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ አሳወቀ። በበጀት ዓመቱ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል የተፈጥሮ ማዳበሪያ ትልን በመጠቀም ስለመዘጋጀቱም ተመላክቷል።

በቢሮው የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክተሩ አቶ እሸቱ ለገሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ክልሉ ለተፈጥሮ ማዳበሪያ ዝግጅት

ክልሉ በተፈጥሮ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## በደምበል ሐይቅ የሚከናወነው የጥምቀት በዓል ትልቅ የቱሪስት መስህብ እየሆነ ነው

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- በባቱ ከተማ ደምበል ሐይቅ ላይ የሚካሄደው የጥምቀት በዓል አከባበር ትርዒት በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶችን እየሳበ መሆኑንና ዘንድሮም ለበዓሉ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን የባቱ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ አህመዲን እስማኤል ገለጹ። በዓሉ በተሻለ የጸጥታ ሁኔታ እንዲከበር በከተማው አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጓል።

አቶ አህመዲን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳመለከቱት፤ የቱሪዝም ከተማ በሆነችው ባቱ በሚገኘው የደምበል ሐይቅ ላይ የሚደረገው የጥምቀት በዓል ትርኢት ሳቢና ታሪካዊ በመሆኑ በርካታ ቱሪስቶች ይገኛሉ።

በደንበል ሐይቅ ላይ የሚከናወነው የጥምቀት በዓል ትርዒት በአይነቱ ልዩ ነው ያሉት አቶ አህመዲን፤ በዓሉ ከአምናው በበለጠ መልኩ በድምቀት እንዲከበር የተለያዩ

በደምበል ሐይቅ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል












ዜና



ኢንጅነር መላኩ እዘዘው

# የግብርና እሴት ሰንሰለትን በማጠናከር የግል አምራቾችን የሚያግዝ ፕሮጀክት ይፋ ሆነ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከጂአይዜድ ጋር በመተባበር የገጠር የግብርና እሴት ሰንሰለትን በማጠናከር አንድ ሺህ የግል አምራቾችን የሚያግዝ ፕሮጀክት ይፋ አደረገ።

የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ኢንጅነር መላኩ እዘዘው በወቅቱ እንደገለጹት፤ ፕሮጀክቱ በግል የተሰማሩ አምራቾችን ለመደገፍና የቢዝነስ ፖሊሲ ትግበራ በተለይም የሽንኩርት፣ አቮካዶና አኩሪ አተር ምርታማነትን ለማሳደግና የገበያ ሰንሰለትን ለመፍጠር ያግዛል፡፡

ለፕሮጀክቱ ትግበራ የተያዘው በጀት 553 ሺህ ዩሮ መሆኑን ጠቅሰው፤ ፕሮጀክቱ በኦሮሚያ፣ አማራና ሲዳማ ክልሎች ይተገበራል ብለዋል፡፡

ለአንድ ሺህ የግል አምራቾች ዘርፈ ብዙና ተከታታይ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው አመላክተው፤ የግሉን ዘርፍ በመደገፍ የግብርና ምርታማነትን የሚጨምር ፕሮጀክቱ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

በሽንኩርት፣ አቮካዶና አኩሪ አተር ምርት ላይ የተሰማሩ ሴቶችና ወጣቶችን ምርታቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያግዝ ፕሮጀክት መሆኑን አመላክተዋል፡፡

ለምርቶቹ ቀልጣፋ የገበያ ሰንሰለት በመዘርጋት የሀገር ውስጥ ገበያው እንዲረጋጋና ምርቶችን በዓለም ገበያ ተፈላጊነታቸው እንዲጨምር እንደሚያደርግ ጠቁመዋል፡፡

ፕሮጀክቱ የግብርና ቢዝነስ ሥራዎች ላይ የማማከርና የፖሊሲ መፍትሄዎች ላይ በጋራ በመሥራት የምክር ቤቱን አቅም የሚያሳድግ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ይፋ የሆነው ፕሮጀክት የምክር ቤቱ ዕቅድ ውጤታማ እንዲሆን እንደሚያግዝ ጠቅሰው፤ ለተግባራዊነቱና ለውጤታማነቱ ምክር ቤቱ የበኩሉን ይወጣል ብለዋል፡፡

የጂአይዜድ ተወካይ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ለሚሳ በበኩላቸው፤ ድርጅቱ የግሉን ዘርፍ አቅምና ምርታማነት የሚያሳድጉ የቴክኒክና ሌሎች ድጋፎችን እያደረገ መሆኑን አንስተዋል።

ፕሮጀክቱ የአቮካዶ፣ የሽንኩርትና የአኩሪ አተር ከምርት እስከ ግብይት ድረስ ያለውን የገበያ ሰንሰለት የመደገፍና ምርታማነታቸውን የማሻሻል እንዲሁም ለክልል ምክር ቤቶችና ማህበራት ሁሉን አቀፍ ሥልጠና በመስጠት ዓላማ እንዳለው ተናግረዋል፡፡

ፕሮጀክቱ እንደሀገር በግብርናው ዘርፍ የፖሊሲ ውይይትና ምክረ ሃሳቦችን ለማቅረብና ውጤታማ ፖሊሲዎችን ለመተግበር የሚደረገውን ሚና በመደገፍ ረገድ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ጨምረው ገልጸዋል፡፡

# "የሚነዙ ጥላቻዎችን በየሺህ ጋብቻ ዓይነት ማህበራዊ መስተጋብሮች መሻር ያስፈልጋል"

- በየሺ ጋብቻ ካርኒቫል የተሳታፉ ጥንዶች

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አዲስ አበባ፡- በተለያየ መልኩ የሚነዙ ጥላቻዎችና የተሳሳቱ አመለካከቶች በየሺህ ጋብቻ ዓይነት ማህበራዊ መስተጋብሮች መሻር እንደሚስፈልግ በሚኒሊየም አዳራሽ ጋብቻቸውን የፈጸሙ ጥንዶች ተናገሩ፡፡

"ቤተሰብን መመሥረት ሀገርን መገንባት ነው" በሚል መሪ ሃሳብ ሁለተኛው የሺህ ጋብቻ ካርኒቫልና ኤክስፖ ሁለት ሺህ ሙሽሮች በተገኙበት በሚኒሊየም አዳራሽ ተካሂዷል፡፡

ከሃዋሳ መጥተው ጋብቻቸውን የፈጸሙት መምህር በላቸው በቀለና መምህርት ፍሬህይወት መኪ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በተለያየ መልኩ የሚነዙ ጥላቻዎችና የተሳሳቱ አመለካከቶች በየሺህ ጋብቻ ዓይነት ማህበራዊ መስተጋብር በሚያስፉ ጉዳዮች መሻር ያስፈልጋል፡፡

የሺህ ጋብቻ መርሃ-ግብሩ የኔ ባህል ብቻ ጥሩ ነው ከሚል አመለካከት በመውጣት የሁሉም ባህል ላይ ያለውን ውበት ማየት የሚቻልበት ነው ብለዋል፡፡

ጋብቻን ከብሔር ብሔረሰቦች ጋር ማክበራቸው ልዩ ስሜት እንደፈጠረላቸው ያነሱት ጥንዶቹ፤ የኢትዮጵያ መልከ ብዙ መሆኗን በተግባር ማየት እንደቻሉ ተናግረዋል፡፡

መርሃ- ግብሩ ባህልን ከማሳደግ ጎን ለጎን ብሔር ብሐሄረሰቦችን በማቀራረብ በጋራ መኖር እንዲችሉ ያግዛል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ሌሎቹ የአዲስ አበባ ነዋሪ ጥንዶቹ ደጀኔ ተፈራና ቅድስት ደስታ በበኩላቸው፤ ሀገር በአንድነት ጸንታ እንድትቆም ልዩነቶችን ወደ ጎን በመተው ማህበራዊ መስተጋብርን ሊያሰፉ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

ጥንዶቹ አክለውም፤ ፕሮግራሙ ማህበራዊ መስተጋብር ከማጠናከር በዘለለ፤ ቱሪዝምን ለማስተዋወቅና ከዘርፉ ገቢ ለማግኘት ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸዋል፡፡

ፕሮግራሙ ለጋብቻ የሚወጣን ወጪ ለመቀነስ ያስችላል ያሉት ጥንዶቹ፤ ጋብቻቸውን ከብሔር ብሔረሰቦች ጋር በማድረጋቸው በልዩነት ውስጥ ያለው አንድነትና ውበት እንዲያጣጥሙ እንደረዳቸው አስታውቀዋል፡፡

የዝግጅቱ አካል በመሆኑ እንዳስደሰተው የገለጸው ደግሞ ሌላኛው ሙሽራ አስፋወሰን አላዩ ነው። በፕሮግራሙ በርካታ የብሔር ብሔረሰቦች ባህልና ባህላዊ ኩነቶች ለመተዋወቅ እንደረዳው ተናግሯል።

በተጨማሪም ከተለያዩ አካባቢው የመጡ አዳዲስ ጓደኞች ማፍራት እንዳስቻለውና ከእርሱ ጋር ጋብቻውን ለማድመቅ የመጡ ዘመድ ጓደኞቹ የሌሎች ሙሽሮችን ቤተሰቦች በመተዋወቅና አብሮነታቸውን በማስፋት ረገድ ምቹ ሁኔታ እንደፈጠረላቸው አስረድቷል።

የሺህ ጋብቻ ካርኒቫል ለሰርግ የሚወጣውን የተጋነነ ወጪ ከመቀነስና አብሮነትን ከማጎልበት ባለፈ በዓለም ድንቃ ድንቅ መዝገብ መስፈር የሚያስችል ዝግጅት መሆኑን ተናግሯል።

# የሴራ መንገሳ የዘመን መለወጫ በዓል በሃላባ ዞን ተከበረ

-የሃላባ ሴራን በዩኔስኮ የዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ እየተሠራ ነው

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**



ሃላባ፡- ጥር 4 እና 5 ቀን 2016 ዓ.ም በሃላባ ዞን ቁሊቶ ከተማ ለሁለት ቀናት ሲከበር የቆየው የሃላባ የዘመን መለወጫ ወይንም ሴራ መንገሳ እሁድ ጥር 5 በተሳካ የአከባበር ሥነ ሥርዓት ተጠናቋል።

ለሁለት ቀናት በቆየው በዚሁ ክብረ በዓል ላይ የሃላባ ሴራ የማንነት መገለጫ የሆነው የመረዳዳትና አብሮ የመበልጸግ እሳቤ (ሚሽላ)፣ የኀዘንና ደስታ መግለጫ (ነቀታ) እንዲሁም የሔቦና በሌሎችም የሴራ የባህል እሴቶች ተንጸባርቀዋል፡፡

የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ሃላፊ ሱልጣን ይማም ሁሴን በዚሁ ወቅት እንደተናገሩት፤ የሴራ መንገሳ የዘመን መለወጫ ወይንም የሃላባ የባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት ማሳያ የሆነው ይህ ክብረ በዓል በማህበረሰቡ ዘንድ በየዓመቱ በጥር ወር የሚከበር ሲሆን ዘንድሮም በድምቀት ተከብሯል፡፡

ከሰባት መቶ ዓመታት በፊት ጀምሮ በማህበረሰቡ ሲከወን የቆየውን የሴራን ሥርዓት የዞኑና የክልሉ ባህል ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ከኢትዮጵያ የቅርስ ጥበቃና ጥናት ተቋም ጋር በመተባበር በሀገርና በዓለም አቀፉ ተቋም ዩኔስኮ በማይዳሰሱ ቅርሶች ዘርፍ ለማስመዝገብ እየተሠራ ስለመሆኑም አቶ ሱልጣን ተናግረዋል።

የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሙህዲን ሁሴን በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መገኛ እንዲሁም የትንሿ ኢትዮጵያ ተምሳሌት የሆነችው የሃላባ ዞን ካሏት እምቅ የማይዳሰሱ ቅርሶች መሀከል፤ የማህበረሰቡ የዘመን መለወጫ የሆነው 'ሀላቢ ሴራ' ወይንም የሃላባ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት አንዱ ነው፡፡

"ሴራን በዓለም የማይዳሰሱ ቅርሶች ስም ዝርዝር ውስጥ ለማካተት ላለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት እራሱን የቻለ ኮሚቴ በማቋቋም ጥናትና ምርምሮችን ስናካሂድ ቆይተናል ያሉት አስተዳዳሪው፤ በየማህበረሰቡ ክፍል ተበታትነው የነበሩትን ልዩ ልዩ እሴቶችንም በማሰባሰብ ወጥነት ባለው መልኩ በአንድ ማህደር እንዲሰፍሩ አድርገናል ብለዋል።

በተለያዩ አካላት ዘንድ የነበሩትንም ልዩነቶች በሰፊ ውይይትና ክርክር ወደ አንድ መግባባት እንዲመጡና ሴራ ሁሉንም ማህበረሰብ በሚያስማማ መልኩ ወደ አንድ እንዲመጣ ተደርጓል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

በሴራ ባህላዊ ሥርዓት መሠረት አፍላ ወጣቶች በዕድሜ በስለው ወደ ሙሉ ወጣትነት ሲሸጋገሩና ለሃላፊነት ብቁ መሆናቸው ሲረጋገጥ የሚከወነው የ 'ሁሉቃ' ሥርዓትም ተከናውኗል።

ለዚህ ብቁ የሆኑ በርካታ ወንድና ሴት ታዳጊዎች በባህል አልባሳቶቻቸው ተውበው የቀጣይ የሕይወት ምዕራፋቸው የሆነውን ማህበረሰባዊ ሃላፊነታቸውን ከአባቶቻቸው ዘንድ ተረክበዋል።

ለሁለት ቀናት በዘለቀው የመንገሳ ሴራ ክብረ በዓል፤ ከአመጋገቡ ሥርዓት እስከ አልባሳት እንዲሁም የማህበረሰቡ የባህል መገለጫ የሆኑ በርካታ እሴቶች የሚያሳዩ ልዩ ልዩ መርሀ ግብሮችን በሁለቱም ቀናት በማከናወን በተሳካ የአከባበር ሥርዓት እሁድ ጥር 5 ቀን ፍጻሜውን አድርጓል።

የሃላባ ሴራ የአንድነት ተምሳሌት እንደመሆኑ ይህንንም ኢትዮጵያዊ የመረዳዳት ባህልን ያንጸባርቀ ክብረ በዓል ነበር ያሉት አስተዳዳሪው፣ በእሁዱ የመዝጊያ ሥነ ሥርዓት ወቅት ሃላባን የሚያዋስኗት ዞኖች በልዑካን ቡድኖቻቸው አማካኝነት በሥፍራው ተገኝተው በዓሉን በጋራ ከማክበራቸውም በላይ ድጋፍ በማድረግ አጋርነታቸውን አሳይተዋል ብለዋል።

ዞኖቹም የእርስ በርስ ትስስር በቋንቋ፣ በባህልና በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮችም አንድነታቸው የጸና መሆኑን በተለያየ መልኩ አሳይተዋል።



# በዓሉ ሰላማዊ ሆኖ እንዲከበር የሰላም ሠራዊት አባላት በትኩረት ሊሠሩ ይገባል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ ፡- በመዲናዋ የመጪው የጥምቀት በዓል ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መልኩ እንዲከበር የሰላም ሠራዊት አባላት በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ በጥምቀት በዓል አከባበር ላይ ከሰላም ሠራዊት አመራር እና አባላት ጋር የማጠቃለያ መድረክ በትናንትናው ዕለት አካሂዷል።

በመድረኩ ላይ የሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ እንደገለፁት፤ ከተማዋ የኢትዮጵያ ብሎም የአፍሪካ መዲና ከመሆኗ ባለፈ ሰፊ ቁጥር ያላው የቱሪስት መዳረሻ ከተማ ናት። በመጪው ጥር 11 የሚከበረው የጥምቀት በዓል ሰላማዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የሰላም ሠራዊት አባላት በትኩረት ሊሠሩ ይገባል፡፡

የአደባባይ በዓላት ሕዝባዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ትውፊት ጠብቀው እንዲከበሩ ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት ወይዘሮ ሊዲያ፤ መጪው የጥምቀት በዓልም ሃይማኖታዊ ትውፊቱን ሳይለቅ ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲከበር የሰላም ሠራዊት አባላት በትኩረት ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

የጥምቀት በዓልም በከተማዋ በሚገኙ ከ270 በላይ ደብራት እና በ78 የታቦት ማደሪያዎች የሚከበሩ መሆኑን ገልጸው፤ ከከተራ ቀን ጀምሮ በዓሉ እስኪጠናቀቅ ድረስ የሰላም ሠራዊቱ ከፀጥታ አካላት ጋር በጋራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

ሃይማኖታዊ በዓሉ ከከተራ እለት በዓሉ እስከሚጠናቀቅበት ዕለት ድረስ ያለምንም ፀጥታ ችግር እንዲከበር የሰላም ሠራዊቱ በትኩረትና በጥንቃቄ መሥራት አለባቸው ሲሉ አሳስበዋል።

የሰላም ሠራዊት አባላት ቅንጅታዊ አሠራር በመፍጠር ለፀጥታ ችግር የሆኑ ጉዳዮችንና መነሻዎችን በመለየትና ማስተካከያ ርምጃዎችን የመውሰድ ተግባራትን በኃላፊነት እንደሚወጡም ገልፀዋል ።

በተለይ ተባብሮ በመሥራት ፣ ብሎም ሕዝብን የሰላም ባለቤት በማድረግ ለሰላም በንቃት እንዲሳተፉ የማስቻል ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባም ወይዘሮ ሊዲያ አሳስበዋል፡፡

የሰላም ሠራዊቱ የፀረ ሰላምና የሽብር ሃይሎች አፍራሽ እንቅስቃሴና የሕግ ጥሰት ስጋት ሲያጋጥም መረጃውን ለሚመለከተው የፀጥታ አካል በማሳወቅ ከሌሎች የጸጥታ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት ይኖርበታል ብለዋል፡፡

ከሰላም ሠራዊቱ በተጨማሪ ሁሉም የከተማዋ ነዋሪዎች ሰላምን ለማስፈንና ለማስጠበቅ በባለቤትነት ከጸጥታ አካላት ጋር በጋራ ሊሠሩ እንደሚገባም ኃላፊዋ አመላክተዋል።

# ኢትዮጵያ የወደብ ባለቤት መሆኗ የአክሪዲቴሽን ሥራ ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው ያደርጋል

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የወደብ ባለቤት መሆኗ የአክሪዲቴሽን ሥራ ልዩ ትኩረት እንዲሰጠውና አቅሙም እንዲጎለብት የሚያግዝ መሆኑን ብሎም በሥነልክ በርካታ ተግባራትን ለማከናወን እንደሚያተጋው የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንደወሰን አንዱዓለም በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘቷ መልካም አጋጣሚ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ቀደም ሲል በሰው ወደብ እና በአንድ መንገድ ስንሯሯጥ እና ምርቶችን ወደ ውጭ ሲላኩ ነበር፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ በራሷ ወደብ ምርትና አገልግሎቶችን መላክ ስትጀምር በርካታ ሁኔታዎች ይለወጣሉ፡፡ ምርት ወደ ውጭ የሚልኩ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተቋማትም ይበራከታሉ፡፡ የውጭ ባለሀብቶችም ኢትዮጵያን ለኢንቨስትመንት መዳረሻነት ይመርጧታል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ከኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ምስክርነት የሚፈልግ ማህበረሰብ ይበራከታል፤ በዚህም ሥራ እየበዛ ይሄዳል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ወንደወሰን ገለፃ፤ ከወደቡ ባለቤትነት ጋር ተያይዞ አሁን ባለን አቅም ብቻ ብዙ መራመድ እንደማንችል እናውቀዋለን፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት እየገነባነው ያለውን ህንፃ በፍጥነት አጠናቀን በበቂ የሰው ኃይል ወደ ሥራ ለመግባት ጥድፊያ ላይ ነን፡፡ ስለዚህ በወደቡ አማካይነት ወደ ውጭ የምንልካቸውና ወደ ሀገር ውስጥ ለምናስገባቸው የግብርና፣ ኢንዱስትሪ ምርቶች እና አገልግሎቶች በፍጥነትና በጥራት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አሠራር ይፈጠራል፡፡

የባህር በር ወይንም የወደብ በአጠቃላይ ንግድ ነው ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ “እኛ በዚህ ሴክተር ውስጥ ነን፡፡ ይህ ወደብ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፤ ከየትኛውም ሴክተር በላይ ለኛ ትልቅ አቅም ነው” ብለዋል፡፡




በመሆኑም ዓለም አቀፍ ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ ለመሆን የወደብ መገኘት ብቻ ሳይሆን ሰዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው እየሠሩ መሆኑን የጠቀሱት ም/ዋና ዳይሬክተሩ፤ ድንበሩ እየፈረሰ ባለው ዓለምአቀፋዊነት ውስጥ መሪ ተዋናይ ለመሆን እየተጋን ነው ብለዋል፡፡

ከዚህ ባሻገር የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ላለፉት 13 ዓመታት በርካታ ልምዶችን አካብቷል ያሉት አቶ ወንደወሰን፤ ከአፍሪካ የላብራቶሪ ትብብር እና ዓለም አቀፍ የላብራቶሪዎች ትብብር ጋርም ያለው ወዳጅነት በጣም ጤናማ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራትም በመምጣት ከኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ልምድ እና ተሞክሮ የሚቀስሙ መኖራቸውን ጠቅሰው፤ ሌላው ቀርቶ የህንድ ትልልቅ ድርጅቶች የአክሪዲቴሽን አገልግሎት እንድንሰጣቸው ሥምምነት ፈጽመናል ብለዋል፡፡

ከሶማሊላንድ ጋርም በተመሳሳይ የአክሪዲቴሽን ሥምምነት ለመስጠት እየተሠራ መሆኑን በመጥቀስ፤ ከበርካታ የአፍሪካ ሀገራት ጋር ደግሞ የአክሪዲቴሽን የሥራ ግንኙነት እንዳለ አብራርተዋል፡፡

“አቅማችንም እያደገ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በየዓመቱ አዳዲስ የዕውቅና ወሰኖችን እየጨመረች ነው፡፡ ባለሙያዎቻችንም በአክሪዲቴሽን አገልግሎት ዙሪያ መለስ ማዕቀፍ ውስጥ በደንብ እየሄዱ ነው፤ ልምድም በሰፊው በማካበት ላይ ናቸው” ሲሉ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

በመሆኑም ሀገሪቱ የወደብ ባለቤት መሆኗ የአክሪዲቴሽን ሥራ ልዩ ትኩረት እንዲሰጠውና አቅሙም እንዲጎለብት የሚያግዝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ከ13 ዓመት በፊት የተመሠረተ ሲሆን በዋናነት ብቃትና ተቀባይነት ያለው አገልግሎት የመስጠት ዓላማን ያነገበ ተቋም ነው፡፡





# «በኪነ-ጥበብ ዘርፍ ያሉ እድሎችን አሟጦ ለመጠቀም በቅንጅት መሥራት ያስፈልጋል»

-ነፊሳ አልማኻዲ
የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ዴኤታ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዳማ፡- በኪነ-ጥበብ ዘርፍ ያሉ እድሎችን አሟጦ ለመጠቀም በቅንጅት መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ነፊሳ አልማኻዲ ገለጹ።

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የኪነ -ጥበብ፣ ሥነ-ጥበብና ፈጠራ ልማት ዘርፉን ማሳደግ በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ከኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች፣ ከሚዲያ አካላት እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ትናንት ተካሂዷል።

በሚኒስቴሩ የኪነ -ጥበብ፣ ሥነ-ጥበብና ፈጠራ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ነፊሳ አልማኻዲ እንደገለጹት፤ በኪነ-ጥበብ ዘርፍ ያሉ እድሎችን አሟጦ ለመጠቀም በቅንጅት መሥራት ያስፈልጋል።

መንግሥት ለኪነ- ጥበቡ ዘርፍ ትልቅ ትኩረት በመስጠት እየሠራ ነው ያሉት ወይዘሮ ነፊሳ በዘርፉ የቅንጅታዊ አሠራር ክፍተቶች ይስተዋላሉ ብለዋል።

ኪነ-ጥበብ ማህበራዊ ቀውስን ለማስወገድ፣ አንድነትንና ሰላምን ለማጽናት ጉልህ ድርሻ እንዳለው ጠቅሰው ዘርፉን ለትውልድ እድገትና ለሀገር ግንባታ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ቀደም ሲል የኪነ- ጥበብ ዘርፉ ብዙ ልማታዊና የጀግንነት ጀብዶች እንደተሠራበት የገለጹት ወይዘሮ ነፊሳ፣ ኪነ-ጥበብ ለሀገር ዘላቂ ግንባታ ካለው አወንታዊ አስተዋጽኦ አንጻር ሀገሪቱ መጠቀም ያለባትን ያክል እየተጠቀመች አይደለም ብለዋል።

ኪነ-ጥበብ ከሥራ እድል ፈጠራ አንጻር ጉልህ ድርሻ እንዳለው በመግለጽ የመገናኛ ብዙሃን የሚያሰራጩትን የይዘት ሥራዎች የህብረተሰቡ ባህልና እሴትን በጠበቀ መልኩ መሆን እንዳለበት ወይዘሮ ነፊሳ አሳስበዋል።

የመድረኩ ተሳታፊዎች በበኩላቸው፤ በዘርፉ የመጠቀሚያ መሣሪያዎችን በቀላሉ አለማግኘት፣ ለዘርፉ የተሰጠው ክብር ማነስ፣ የሰላም እጦትና ከጽንፈኝነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በዘርፉ ላይ መዳከምን እንደፈጠሩ ጠቅሰው ከማህበረሰቡ ባህልና እሴት ውጪ የሆኑ ይዘቶች መሰራጨት ኪነ-ጥበቡን እንዲዳከም ካደረጉት ምክንያቶች መካከል እንደሆኑ ተነስተዋል። እንደ ተሳታፊዎቹ ገለጻ፤ ኪነ-ጥበቡን ከወደቀበት ለማንሳት በመንግሥት አስቻይ ሁኔታዎች መፈጠር አለባቸው፡፡

በተጨማሪም የፖሊሲ ማሻሻያና ለዘርፉ ነጻነት መስጠት እንዳለበት በተሳታፊዎቹ እንደ መፍትሔ ተነስተዋል።

“የኪነ-ጥበብ ሥራዎች ባህል፣ እሴት፣ አንድነት እንዲሁም ሰላምን ከመጠበቅ አንጻር የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችና የባለድርሻ አካላት ሚና” በሚል መሪ ሃሳብ በተዘጋጀው የምክክር መድረክ የኪነ-ጥበቡ ዘርፍ ያለው አወንታዊ ሚና አሟጦ ለመጠቀም በቅንጅት መሥራት እንዳለበት በመድረኩ ተመላክቷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስምምነቱ ዘመኑን ከሚዋጅ ዓለም አቀፍ እሳቤ የተቀዳ ነው!

አሁን ላይ ዓለምን ወደ አንድ መንደርነት ለማምጣት በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ዘርፎች ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። የታሰበውን ያህል መጓዝ ባይቻልም አስተሳሰቡ ፣ እንደአስተሳሰብ ዘመኑን የሚዋጅ ስለመሆኑም ብዙ ተብሎለታል። የብዙዎችን ቀልብ በመሳብም ዓለም አቀፍ የመነጋገሪያ አጀንዳ ከሆነ ዓመታት አልፈዋል።

በጉዳዩ ላይ ብዛት ያላቸው ጥናትና ምርምሮች ተካሂደዋል ፤ አስተሳሰቡ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኝ ብዙ መድረኮችም ተዘጋጅተዋል። መንግሥታትና ዓለም አቀፍ ተቋማት ዋነኞቹ የሃሳቡ አራማጆች በመሆን ረጅም ርቀት ተጉዘዋል። በጉዳዩ ዙሪያ ሰባኪና ጉዳይ አስፈጻሚ ሆነው ባላቸው አቅም ሁሉ ሲንቀሳቀሱም ተስተውለዋል።

ዓለም ከልዩነት ይልቅ በአንድነት ብዙ ልታተርፍ እንደምትችል ፤ ይህ አንድነት ዓለም አቀፍ ገጽታ እየተላበሰ ሲመጣ ፤ ምድራችን ለነዋሪዎቿ የተሻለች የመኖሪያ ሥፍራ እንደምትሆን ፤አሁን ላይ እያጋጠሟት ያሉትን መልከ ብዙና ውስብስብ ችግሮች በጋራ ለመፍታት እንደሚያስችልም እሳቤው ዙሪያ የተደረጉ የተለያዩ ጥናቶች አረጋግጠዋል።

አሁን ላይ አስተሳሰቡ በብዙ ፈተናዎች ጫና ውስጥ ቢሆንም ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና በማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ፤ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራዎች በአንድም ይሁን በሌላ ይህንን አስተሳሰብ ታሳቢ ያደረጉ ፤ ለአስተሳሰቡ ተገዥ የሆኑ፤ ለአስተሳሰቡ ዓለም አቀፍ መሠረት መጣል የሚያስችሉ ናቸው።

ይህ ዓለምን ለነዋሪዎቿ የተሻለች ለማድረግ ፤ የተጀመረው ዓለም አቀፍ ንቅናቄ የጋራ ተጠቃሚነትን እና የጋራ ዕጣ ፈንታን በጋራ መሥራት ላይ መርህ ያደረገ ነው። በዚህም ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ በብዙ ጥያቄዎች ውስጥ ሆኖ አሳቤው ፤ ከዛሬ ፈተናዎቹ በስኬት አሻግሮ፤ የተሻሉ ነገዎች ይዞለት እንደሚመጣ ተስፋ እያደረገ ነው።

አስተሳሰቡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍ ባለ ድምጽ ከመሰማቱ የተነሳም ፤ ሀገራት ለአሁናዊ ችግሮቻቸው ሆነ ለነገ ስጋቶቻቸው፤ በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚ እና በማኅበራዊ ዘርፎች መቀራረብን በመፍጠር ዘላቂ እና ስትራቴጂክ የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እየሠሩ ነው።

ለዚህም በኢትዮጵያና በሶማሊላንድ መካከል ሰሞኑን በወደብ አጠቃቀም ዙሪያ የተደረሰበት የመግባቢያ ስምምነት ተጠቃሽ ነው። ስምምነቱ በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ፤ ከሁሉም በላይ በሕዝቦቻቸው መካከል የነበረውን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ሊያሳድግ የሚችል ነው።

ቀደም ሲል በመካከላቸው የነበረውን የወንድማማችነት መንፈስ በብርቱ መሠረት ላይ ፤ በተሻለ መልኩ የሚገነባበትን መልካም አጋጣሚ የፈጠረ ፤ የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ባደረገ በሰጥቶ መቀበል መርህ ፤ ግንኙነታቸውን ወደ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ማሸጋገር የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል ።

ስምምነቱ የአካባቢው ሀገሮች ካልተገባ ጥርጣሬና ማንንም ሊጠቅም ከማይችል የሴራ ፖለቲካ ወጥተው አካባቢው አዲስ የኢኮኖሚ አቅም ሆኖ የሚፈጠርበትን ዕድል የሚያመቻች፤ የአካባቢው ሀገራት ዕጣ ፈንታቸው የተሳሰረ መሆኑን ነገ ላይ በተጨባጭ ማሳየት የሚያስችል ነው።

የቀጣናው ሀገራት በዓለም አቀፍም ሆነ በአካባቢያዊ መድረኮች የተሻለ ተደማጭነት እንዲኖራቸው ፤ በዚህም ብሔራዊ ጥቅሞቻቸውን በተሻለ መንገድ ማስጠበቅ የሚችሉበትን መልካም አጋጣሚ መፍጠር የሚያስችል ትልቅ ተጨባጭ ተሞክሮ ሊሆን የሚችል እንደሚሆንም ይታመናል።

የመግባቢያ ስምምነቱ ከዚህም ባለፈ ዓለም ዘመኑን ይዋጃል ብሎ ዛሬ ላይ ብዙ ከመናገር አልፎ ስለተግባራዊነቱ ብዙ ርቀት እየተጓዘበት ካለው ዓለምን ወደ አንድ መንደር የመለወጥ አሳቤ የሚጣጣም ፤ በጋራ በመቆም የተሻለ ተጠቃሚነትን መፍጠር በመሆኑ ሊበረታታ የሚገባ ትልቅ ስኬት ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ትኩረት የሚሻው በምግብ ሸቀጦች ላይ የሚጨመሩ ባእድ ነገሮች ጉዳይ

በምግብና ምግብ ነክ በሆኑ ነገሮች ላይ የሚጨመሩ ባዕድ ነገሮች በጤና ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት እጅግ ከፍተኛ ነው። ከዚያ ባሻገር በኢኮኖሚ፣ በንግድ ልውውጥና በሌሎች ጉዳዮች ላይ በርካታ ጥፋቶችን ያደርሳሉ። ይህንን ወንጀል ለማስቀረት የሚደረግ ቁጥጥርና ክትትል ሥራ ጠንካራ ካልሆነ ሊያስከትል የሚችለው ሁለንተናዊ ጥፋት ለመገመት የሚከብድ ነው።

ኢትዮጵያውያን በባህል፣ በእምነት ጠንካራ ሥነ ምግባር ያለን ሕዝቦች ነን። እንግዳን ተቀብሎ አልጋውን ለቅቆ፣ እግሩን አጥቦ የሚያስተናግድ የሀገሬው ሕዝብ በንግዱም ዓለም ተመሳሳይ የሞራል ልእልና ይዞ ለዘመናት የቆየ ነው። አይደለም ባእድ ነገር ሊጨምር ከህቁ ፈቀቅ ብሎ ትርፍን የማይሻ ነበር። አሁን አሁን ግን ይህንን ባህል ለመሸርሸር የሚጣጣሩ ጥቂት ሕገወጥ ነጋዴዎች እየተመለከትን ነው።

በመገናኛ ብዙሃንና በዲጂታል ሚዲያው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዚህ ሕገወጥ ተግባር የሚሳተፉ ግለሰቦች እየተበራከቱ ስለመምጣታቸው በስፋት ሲነገር እየሰማን ነው። ችግሩ በተለይ በአውድ ዓመት አካባቢ፤ የበዓላትን ገበያ ታሳቢ በማድረግ ሊበራከት እንደሚችል ለመገመት የሚከብድ አይደለም። ለዚህ ማሳያ የሚሆነኝ አንድ ጉዳይም ከሰሞኑ በአዲስ አበባ የካቲት 12 ሆስፒታል አካባቢ ገጥሞኝ ነበር።

በመገናኛ ብዙሃንና በልዩ ልዩ አማራጮች የምንሰማቸው ጆሮን ጭው የሚያደርጉ ሕገወጥ ድርጊቶች አንፃር እኔን የገጠመኝና ለትዝብት ያበቃኝ አጋጣሚ እንዲሁ በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም። ለዚህ ነው በዛሬው ርእሰ ጉዳይ ላይ ለጥንቃቄ እንዲረዳ ርእሰ ጉዳይ አድርጌ ወደናንተ ይዤው የመጣሁት።

ባሳለፍነው ሳምንት በአንዱ ቀን በሆስፒታሉ አካባቢው እያለፍኩ በድንገት በጥቁር ፌስታል ምንነቱ ያልታወቀ ነገር ያንጠለጠለ ሰው ጎሸም አደረገኝ። ዞር ብዬ ተመለከትኩት። ካለባበሱና ከሁኔታው አንፃር ሲታይ ከክፍለ ሀገር በቅርብ የመጣ ከሚመስል ሰው ጋር ተፋጠጥኩ። የአነጋገር ለዛው ግን የከተማው ጩልሌዎችን ያስንቃል። ጊዜ ሳላባክን ምን እንደፈለገ ጠየቅኩት። የያዘው ቅቤ እንደሆነ ገልጾ ወደ እኔ እያስጠጋው እንድገዛው ጠየቀኝ።

በጠራራ ፀሐይ ቅቤን ያክል ነገር ይዞ በመዞር ግዙኝ እያለ ሲንከራተት አለመቅለጡ ገረመኝ። ስለ ሁኔታው ለማወቅ ጉጉት አደረብኝ። ሁኔታው እያጠራጠረኝም በአትኩሮት ቅቤውን ተመለከትኩት። መልኩ ቅቤ ይመስላል። ጎንበስ ብዬ አሸተትኩት። ምንም የቅቤ ሽታ የሚባል ነገር የለውም። የሻጩንና የእኔን ሁኔታ የተመለከቱ ሰዎች ተቀላቀሉን። በተመሳሳይ እነርሱም አሸተቱት። የቅቤ ሽታ እንደሌለው ምስክርነታቸውን ሰጡ።

ቅቤ ከያዘው ሰው ጋር አብሮ ሌላም ሰው አለ። እርሱም ማር መያዙን እየነገረን እንድንገዛው ጠየቀን። ማሩ ቅልጥልጥ ያለ ነገር ነው። በዙሪያችን ብዙ ሰዎች አሉ።

ከእነርሱ መካከል አንዷ ባለቅቤውን እውነተኛ ንፁህ ቅቤ ከሆነ በዚህ ጠራራ ፀሐይ ለምን እንደማይቀልጥ ጠየቀችው። ፌስታል ስለደራረበበትና ውሃ ስለነከረው መሆኑን ጠቅሶ ሊያብራራላት ሞከረ፤ በሃሳቡ መስማማት ግን አልቻሉም።

ይብሱኑ «ምን አገባሽና ነው ገበያዬን የምታበላሽው ፤ ከገዛሽ ግዢ ካልገዛሽ ተይው» የሚል ሀይለቃል ተናገራት። ጉዳዩ ከግዢ ድርድር ወጥቶ ወደ ግብግብ ተለወጠ። ሊገዙት የከበቡትም ነገሩ ስላላማራቸው ጥለውት ሄዱ። በዚህ መካከል በርካታ ሰው ሲሰበሰብና ፖሊስ እጠራለሁ ስትል ማርና ቅቤ ግዙን ባዮቹ የከበብናቸውን እየገፈታተሩ ወደ ጃን ሜዳ እግሬ አውጪኝ አሉ።

የያዙት ቅቤና ማር ጤናማ ቢሆን ፤ አንዳች በአድ ነገር የተቀላቀለበት ባይሆን በሩጫ እንደማይሸሹ መገመት የሚከብድ አይደለም። በአድ ነገር የተቀላቀለበት ቅቤና ማር ገዝተው እንደከሰሩ የሚናገሩ ብዙ ሰዎች ስለገጠሙኝ ግምቴ፤ ግምት ብቻ እንዳልነበር ለማረጋገጥ አልከበደኝም።

ለረጅም ቀናት ተቀምጦ የማይሻግትና የማይበላሽ በርበሬ እና ሽሮ፤ መታጠፍና መቆረጥ ቀርቶ ለመጉረስ በእጅ እንኳን ለመቁረስ ሲሞከር ባለበት ተፈረካክሶ የሚቀር እንጀራ መግዛታቸውን በግርምት ሲናገሩ ያደመጥኳቸው አሉ። በገበያ ላይ ምንም ያህል ወተት የሚፈለግበት ወቅት ቢሆን ሰርክ የማይጠፉባቸው ሱቆች መበራከታቸውንም ታዝቤያለሁ። ከነዚህ ሱቆች የሚገዛው ወተት ለፈለገ ቀናት ቢቀመጥ እንደማይረጋ የማየቱም ዕድል ገጥሞኛል።

ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ ባዕድ ነገር የሚቀላቀልባቸው ምግቦች ሆኑ ምግብ ነክ ነገሮቹ ከቀላል እስከ ከባድ የጤንነት ችግር የሚዳርጉ ናቸው። ካንሰርን ጨምሮ ሌሎች ለረጅም ጊዜ ስር የሚሰዱ የጤና ችግሮችን ሊያስከትሉ ይችላሉ።

ባዕድ ነገሮቹ የመቀላቀሉ ተግባር ከተራ ማጭበርበር ውጪ ለሁለት ምክንያቶች ይከናወናሉ። አንደኛው ምግቡ ወይም ምርቱ ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ ለማስቻል ነው። ለምሳሌ ወተትን ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ ለማቆየት ሲባል ፎርማሊን፣ ሀይድሮጅን ፐሮክሳይድ እና ሌሎችም ከፍተኛ የጤና ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ ጎጂ ኬሚካሎችን የሚጨምሩ እንዳሉም የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በጉዳዩ ዙሪያ ያጠናቸው በቤተ ሙከራ የተደገፉ ጥናቶች ያትታሉ።

ሁለተኛው ዓላማ ለዓይን እይታ ማራኪና ሳቢ እንዲሆኑ ለማስቻል የሚጨመሩ ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞም የኢንስቲትዩቱ ጥናት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለምግብ ቀለምነት እንዳይውል የተከለከለና «ዳይ» የተሰኘ ኬሚካል የሚቀየጥበት ሁኔታ እንዳለም ያመለክታል።

ኢንስቲትዩቱ በቅርቡ በሀገር ደረጃ ከ300 በላይ በሽታዎች ላይ ጥናት ማድረጉን ይፋ አድርጓል። በጥናቱ ይፋ ካደረጋቸው በሽታዎች መካከል የደምን ጨምሮ ካንሰር፣ የኩላሊት ኢንፌክሽን የልብ ህመምና ሌሎች የረጅም ጊዜና ስር የሰደደ የጤና ችግርን የሚያስከትሉ ተጠቃሽ ናቸው። ለበሽታዎቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ዋነኛው ምክንያት በምግቦች ላይ የሚጨመሩ ባዕድ ነገሮች ስለመሆናቸው አመልክቷል።

በነገራችን ላይ በሀገራችን ብዙ ቦታዎች እንደየአካባቢው ባህልና አኗኗር ዘይቤ ምግብና ምግብ ነክ ነገሮች ውስጥ ሊቀራረቡ የሚችሉ የእህል ዘሮችን መቀላቀል የተለመደ ነው። ለአብነት ብንጠቅስ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል እንጀራ ከጤፍ፣ ከማሽላ፣ ከበቆሎ ጋር ተቀላቅለው ለምግብነት ይውላሉ። ከስንዴ ዱቄት ጋር ሊቀራረቡ የሚችሉ የእህል ዓይነቶች ሊቀላቀሉ ይችላሉ።

ወደ ደቡቡ የሀገራችን ክፍል ለምሳሌም አርባ ምንጭና ወላይታ ስንሄድ ደግሞ ሥራ ስሮች ተቀላቅለው ለምግብነት ይቀርባሉ። ቦዬ እና ጉደሬ ከሚቀላቀሉት ውስጥ ይጠቀሳሉ። በተለይ ቦዬ የሚባለው ስራስር ሲፈጭ ንጣቱ ልክ እንደ ጀሶ በመምሰሉ እንጀራውን ባዕድ ነገር የተቀላቀለበት ነው ብለን ብንጠረጥር አይፈረድብንም። እንጀራው አቅም እንዳይኖረውና ሳይቆርሱት እንዲፈረካከስ ሊያደርግም ይችላል።

ከእነዚህ ጋር ተያይዞ ከሕብረተሰቡ ወደ ፖሊስ የሚመጡም ብዙ ጥቆማዎች መኖራቸውንም መረጃዎች ያሳያሉ። መረጃዎቹ ቦዬን እንጀራ ውስጥ መጨመር ከጥራት ጋር ተያይዞ ቅሬታዎች የሚነሱበት እንዳለም ይጠቁማሉ። ለፖሊስ ሪፖርት ተደርገውም ቦዬ የተቀላቀለበት ሊጥ ከነቦሃቃው እጅ ከፍንጅ የተያዘበትም አለ። ሆኖም በተደጋጋሚ በነዚህ ላይ የቤተ ሙከራ ፍተሻ ተደርጎ ከተለመደው የእንጀራ ባህርይ ውጭ አልታየባቸውም። ግን የተለየ ባህርይ አልታየባቸውም ተብለው የሚታለፉ አይደሉም።

ኢንስቲትዩቱን በቀጥታ የሚመለከተው ለጤና ጠንቅ የሆነውን መለየት ከሚያስችል ጥናትና ምርምር ጋር የተያያዘው ብቻ ነው። ቢሆንም ይህም የጤፍ አስመስሎ የቦዬ እንጀራን ለገበያ የማቅረብ ጉዳይ ማህበረሰቡን ከማጭበርበር ጋር ተያዞ መፍትሄ ሊፈለግለት የሚገባ ነው። መሰል ሕገወጥ የወንጀል ተግባርን ፖሊስና እና የኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን በትኩረት ሊሠሩበት ይገባል።

በአዲስ አበባ የተደረገው ፍተሻ በከተማዋ እንጀራ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ጀሶ፤ ሰጋቱራ እና ሌሎች በአድ ነገሮች የሚቀይጡ የሉም የሚለውን አያሳይም። በሆኑም በጉዳዩ ዙሪያ ተጨማሪና ሰፋ ያለ ጥናት የሚጠይቅ ሆኖ ተገኝቷል። ኢንስቲትዩቱ ዘንድሮ በዚህ መልኩ አዲስ አበባ ላይ ያካሄደውን በቤተ ሙከራ የተደገፈ ፍተሻ ሰፋ አድርጎ በ11 ክልሎችና በተመረጡ 24 ከተሞችም በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲያካሂድም መሰንበቱን ነግሮናል።

ፍተሻው የተካሄደው ባዕድ ነገሮች ሊቀላቀሉባቸው ይችላሉ ባላቸውና ማህበረሰቡ ተደጋጋሚ ቅሬታ እያቀረበባቸው ባሉ ዘጠኝ ምግቦች እና ምግብ ነክ ሸቀጦች ላይ ነው። 4000 የእነዚህን ምግቦች ናሙናም ተጠቃሚ በመምሰል በተመራማሪዎቹ ተሰብስቧል።

እንደ መረጃው ከሆነ ከተሰበሰቡት ናሙናዎች መካከልም ሕብረተሰቡ አዘወትሮ የሚጠቀምባቸው እንጀራ፣ ዳቦ፣ ስንዴ ዱቄት፣ ወተት፣ ማር፣ ቅቤ ይገኛሉ። በቤተ ሙከራ ተደግፎ በመጀመር 2025 የሚዘልቅ ጥናትና ምርምር በስጋ አቅርቦት ላይ የሚሰሙ ሀሜቶችንም የሚያካትት ስለመሆኑ ግምት አለ።

ከላይ ካነሳሁት መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው በአድ ነገር በምግብ ምርቶች ላይ የሚቀላቅሉ ሕገ ወጦች መኖራቸውን ነው። ይህ ከሞራል ያፈነገጠ ተግባር ማህበረሰቡን ለጤና ቀውስ ከመዳረጉም ባለፈ ለህክምና ከፍተኛ ያጋልጣል። ከዚህ ባሻገር የማህበረሰቡን የሥነምግባር፣ ባህልና የሞራል ልእልና የሚሸረሽር ጠንቅ ነው።

በበዓላት ወቅት ኢትዮጵያውያን በብዛት ለምግብ የሚውሉ ምርቶችን ወደ ገበያ ወጥተው ይሸምታሉ። በብዛት ግዢና ሽያጭ በመከናወኑ ምክንያት ማጭበርበሮችም አይጠፉም። በዚህ ምክንያት ለከፋ የጤናና የኢኮኖሚ ችግር የሚያጋልጡ በአድ ምርቶች ያጋጥሙናል። ለዚህ ችግር ላለመጋለጥ ሸማቹም ሆነ ተቆጣጣሪ የመንግሥት አካላት ትኩረት በመስጠት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። ከፍተኛ ጥንቃቄንም መውሰድም ያስፈልጋል።

በሕገወጥ ተግባሩ የሚሣማሩ ግለሰቦችን ፍትህ ፊት ማቅረብም አንዱ መንገድ ነው። አጠራጣሪ ነገር ሲታይ ለሕግ አስከባሪ መጠቆም እራስን ከመጭበርበር ከማዳኑም በቀጣይ እንዳይደገም ማስተማሪያ ስለሚሆን ሁላችንም ዘብ መሆን ይገባና እላለሁ። ሰላም!!

# ተጠየቅ

# ‹‹በአክሪዲቴሽን ከመጣነው መንገድ ይልቅ፤ የምንሄድበት መንገድ ይርቃል››

**አቶ ወንድወሰን አንዱዓለም**
**የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር**

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

ከ13 ዓመት በፊት የተመሰረተው የኢትዮጵያ አክርዲቴሽን አገልግሎት ዘርፈ ብዙ ተግባራትን የሚያከናወን ነው፤ በዋናነት ብቃትና ተቀባይነት ያለው አገልግሎት የመስጠት ዓላማ ያነገበ ነው፡፡ በተለይም በውጭ እና ገቢ ምርቶች ላይ የሚሰራቸው ሥራዎች ከሀገሪቱ አጠቃይ ገፅታ ጋርም የሚያያዝ ነው፡፡

ተቋሙ የኢትዮጵያን ምጣኔ ሃብት ዕድገት በሚያፋጥኑ ዘርፎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ላይ ነው፡፡ የዝግጅት ክፍላችንም በዛሬው ዕትሙ የተቋሙን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴዎች፣ ቀጣይ እቅዶች እና አሁናዊ ክንውኖች በተመለከተ ከተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ወንድወሰን አንዱዓለም ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት አሁናዊ ቁመና ምን ይመስላል?**

**አቶ ወንድወሰን፡-** የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ለመጀመሪያ ጊዜ በ2003 ዓ.ም በኋላም ተጨማሪ ኃላፊነት እና ተልዕኮ ተሰጥቶት 2010 ዓ.ም በአዋጅ የተቋቋመ ተቋም ነው፡፡ ሲቋቋም በዋናነት ብቃትና ተቀባይነት ያለው አገልግሎት መስጠትን ዓላማ አድርጎ ነው፡፡

ተቋሙ አሁን ያለውን ቁመና ከመያዙ በፊት እንደ ሀገር የግብርና እና የኢንዱስትሪ፣ ምርቶችና አገልግሎቶች አክርዴትድ የሚሰጠው በውጭ ሀገራት ነበር፡፡ ይህ ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል፡፡ አገልግሎቱ በዋነኛነት የተቋቋመውም ከሀገር ውስጥ የሚወጡትንም ሆነ የሚገቡትን ምርትና አገልግሎት በዋናነትም የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶች ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ፣ በዚህም ሕዝብና ሀገር ማግኘት ያለባቸው ጥቅም እንዲያገኙ ለማስቻል ነው፡፡

አገልግሎት የተቋቋመው በሀገር አቀፍ ደረጃ እጅግ አንገብጋቢ የሆኑ ጥያቄዎች በመኖራቸው ነበር። ተቋማችንም አሁን ላይ እየተንቀሳቀሰ ያለው በዚህ ደረጃ ሁኔታዎችን ተገንዝቦ ነው፡፡ አክሪዲቴሽን ስንል አንድ ተቋም ሥራው እና አገልግሎቱን በአግባቡ ስለመወጣቱ የሚሰጥ ምስክርነት ነው፡፡ ይህ ምስክርነት ካልተሰጠ በስተቀር ተቋማት ምርትና አገልግሎታቸውን ይዘው ከሀገር ሊወጡ አይችሉም። በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ እና ተፈላጊ የመሆን ዕድላቸውም ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህን እውን ለማድረግ ተቋሙ እንደሀገር ተመስርቶ ወደ ሥራ ገብቷል። በዚህም ቀደም ሲል ይወጣ የነበረን የውጪ ምንዛሪ ማዳን፤ ውጤታማ መሆንም ተችሏል፡፡

ተቋሙ 2004 ዓ.ም በሙሉ አቅሙ ሥራ በመጀመር ፈጣን እምርታ በማሳየት ዓለም አቀፍ የላብራቶሪዎች ትብብር ዕጩ አባል ሆኗል፡፡ ይህ በመሆኑም የኢትዮጵያ አክርዲቴሽን አገልግሎት ጋር በቅርበትና በጋራ ተደጋግፎ የመስራት ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡ በመቀጠልም ለክልል መንግስታት፣ ለከተማ አስተዳደሮች፣ ለሕግ ተርጓሚዎች እና አስፈፃሚዎች እና የተለያዩ አካላት ሥራውን ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

በመጨረሻም የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት በ2009 ዓ.ም ዓለም አቀፍ የላብራቶሪዎች ትብብር አባል ሆኗል፡፡ ይህ ስኬት የመጣው በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለያዩ ባለሙያዎችን ወደ ኢትዮጵያ በመላክ ማረጋገጫዎች ከተሰሩ በኋላ ነው፡፡ ለዚህም በተቋሙ ውስጥ የነበሩ አመራሮች እና ባለሙያዎች በርካታ ስኬታማ ሥራዎች አከናውነዋል፤ ሊመሰገኑም ይገባል፡፡

ቀደም ሲል የአክሪዲቴሽን ሥራ ይሰራ የነበረው በሕክምና ላብራቶሪ እና በፍተሻ ላብራቶሪ ላይ ብቻ ነበር፡፡ በሂደት ፈጣን እምርታ በማሳየት በኢንስፔክሽን አክርዲቴሽን ተጨማሪ ዓለም አቀፍ እውቅና ተገኝቷል። ለዚህም በ2014 ዓ.ም በጥራት ሥራ አመራር ሰርተፊኬሽን እና በ2015 ዓ.ም ደግሞ በሥነ-ልክ ካሊብሬሽን ላብራቶሪ ወሰኖች ዓለም አቀፍ ዕውቅና አግኝተናል፡፡

**ቀደም ሲል በሰው ወደብ እና በአንድ መንገድ ስንሯሯጥ እና ምርቶችን ወደ ውጭ ስንልክ ነበር፡፡ ነገር ግን በራሳችን ወደብ ምርትና አገልግሎቶችን መላክ ስንጀምር ፍሰቱ አሁን ካለው መጠን ይጨምራል፡፡ ምርት ወደ ውጭ የሚልኩ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተቋማትም ይበራከታሉ**


ፎቶ ዳኜ አበራ

በእርግጥ እንደ ሀገር አንዴ የተሰጠ ዓለም አቀፍ ዕውቅና በዓለም ገበያ ውስጥ ዘላለማዊ አይደለም። በየጊዜው ዓለም አቀፍ የላብራቶሪዎች ትብብር ባለሙያዎች እየተላኩ ምልከታ ያደርጋሉ፤ ይገመግማሉ። በቂ ሆኖ ካልተገኘ አንዳንዱን እውቅና ሊሰርዙ ይችላሉ፡፡ እኛ እስካሁን የተሰረዘብን እውቅና የለም። ካለን በተጨማሪ ሌሎች ዓለም አቀፍ እውቅናዎችን አግኝተናል፡፡ በዚህም ደንበኞቻችን ሳይጉላሉ እየተስተናገዱ ነው፤ ሀገርንም ከወጪ መታደግ ችለናል።

**አዲስ ዘመን፡- ሀገሪቱ ካላት የምጣኔ ሃብት ዕድገት፣ የደንበኞች ፍላጎት እና ሌሎች ሁኔታዎች አኳያ የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት በቂ ነው ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ወንድወሰን፡-** በተለያዩ ምክንያቶች በቂ ነው ማለት አንችልም፡፡ የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያገኘንባቸው ወሰኖች ውስን ናቸው፡፡ ሌላው አገልግሎቱ አስገዳጅ ባለመሆኑ ነው፡፡ የእኛ ደንበኛ በእኛ አክርዲት ለመደረግ አይገደድም፡፡ በማንኛውም ተቋም አክርዲትድ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ አካሄዶች አስቸጋሪ ቢሆኑም፤ በዚያው በተለመደው አካሄድ መሄድን የመምረጥ አዝማሚያ አለ፡፡ በኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት የግድ እውቅና ወይንም ምስክርነት ሊሠጥ ይገባል የሚል መመሪያ ወይንም አዋጅ ባለመኖሩ እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮች አሉ።

በአክሪዲቴሽን ዙሪያ የግንዛቤ እጥረት አለ። የጥራት ጉዳይ ሲነሳ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ መስፈርቶቹ፣ ሳይንሱ እና ሌሎች መለኪያዎቹ ውስብስብ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም በዘርፉ በቂ የተማረ የሰው ኃይል በሀገር ውስጥ አለመኖር ለስራው ተግዳሮት እየሆኑ ነው።

ለምሳሌ የውጭ እና ውስጥ አሰሰርስ (external and internal assessors) የምንላቸው አሉ፡፡ አሰሰርስ የምንላቸው ምስክርነት የሚፈልገው ተቋም ወይንም ከእኛ ምስክርነት የፈለገው ተቋም በተለያዩ መመዘኛዎችና ልኬቶች መዝኖና ተንትኖ ለተቋማችን ማናጅመንት አቅርበው እውቅና እንዲያገኝ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

ሌላው ውስጣዊ አሰሰርስ (Assessors) ናቸው ፤ለነዚህ በቂ ደሞዝ መክፈል፤ ባለመቻላችን ለተሻለ ደመወዝ ወደሌላ አካባቢ ይፈልሳሉ፡፡ የውጭዎቹም በትክክል የሚመጣጠን ክፍያ ስለማያገኙ በሚጠበቅብን ልክና መጠን እያገለገልን ነው የሚል እምነት የለኝም፡፡ ይህም ቢሆን ግን የመጣንበት የስኬት መንገድ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ግን በአክሪዲቴሽን ከመጣነው መንገድ ይልቅ የምንሄድበት መንገድ ይርቃል፡፡ ካስመዘገብነው ድል ይልቅ ወደፊት የምናስመዘግበው ድል እንደሚበልጥ እናምናለን፡፡ በቂ የሰው ኃይል እንዳንቀጥር ከሚፈትኑን ችግሮች መካከል በቂ የሕንፃ መሰረት ልማት አለመኖር ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት እየገነባነው ያለው ሕንፃ አሁን ካለን የሠው ኃይል በአራት እጥፍ ለመቅጠር ያስችለናል፤ መዋቅሩም ይፈቅድልናል።

**አዲስ ዘመን፡- ደንበኞች በእናንተ አክርዲት ስመደረግ አስመገዳዳቸው እንደ ተቋም የሚፈጥረው ችግር እና እንደ ሀገር የሚያሳጣው ጥቅም አለ?**

**አቶ ወንድወሰን፡-** አዎ! አለ፡፡ ሀገሪቱ ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ እንረዳለን፡፡ ትኩረታችን በብዛት ወደ ውጭ የሚወጡ ምርቶች ላይ ነው፡፡ የሀገር ውስጥ ምርቶችና አገልግሎቶችም አክርዲት መደረግ አለባቸው። ለምሳሌ የተሽከርካሪዎች ‹‹ቦሎ›› የሚያድሱ ተቋማት መኪናው ብቃት አለው፣ አገልግሎት መስጠት ይችላል

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

# ‹‹በአክሪዲቴሽን ከመጣነው መንገድ...

ከገጽ 6 የዞረ

ብለው ለሚመለከተው አካል ይፅፋሉ፡፡ በመቀጠል ኢንሹራንስ እና የመሳሰሉት ይታደሳሉ፤ ፈቃድም ይሰጣል፡፡

ነገር ግን ተሽከርካሪው ብቃት አለው የሚሉት አካላት በራሳቸው ብቃታቸው ምን ያህል ነው ብለን መጠየቅ አለብን፡፡ የባለሙያዎቻቸው ብቃት እና የማሽኖቻቸው ትክክለኛነት እስከምን ድረስ ነው ለሚለው ሕግ አክርዲትድ እንዲሆኑ አያስገድዳቸውም። ሌሎችም ላይ በተመሣሣይ ነው፡፡ አክሪዲትድ ስሆን እጠቀማለሁ ብሎ ካልመጣ በስተቀር ሥራውን መሥራት ይችላል፡፡ አሁንም ከተሽከርካሪዎች ጋር በተያያዘ በየጊዜው የምንሰማውና የምንመለከተው የትራፊክ አደጋ የሚነግረን ነገር አለ። ተሽከርካሪዎቹ ብቃት አላቸው ብለው የሚመሰክሩ አካላትም ብቃት መፈተሽ አለበት። በመሆኑም በአገር ውስጥ ባሉ ምርትና አገልግሎቶች ላይ አክርዲቴሽን አስገዳጅ ባለመሆኑ ችግሮችን ለማየት እየተገደድን ነው፡፡

የተወሰነ ግንዛቤ ያላቸው ተወዳዳሪ ለመሆንና ብቃታቸው እንዲመሰከርላቸው ወደ ኢትዮጵያ አክርዲቴሽን አገልግሎት ይመጣሉ፡፡ ወደ ውጭ የሚወጡ ምርትና አገልግሎትም ላይ የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት እውቅና ይፈልጋሉ፤ ዓለም አቀፍ ገበያውም ያስገድዳቸዋል፡፡ ካልሆነ ገበያውን ሰብረው መግባት አይችሉም ወይንም ተወዳዳሪ አይሆኑም፡፡ በሕንፃ ግንባታም ሲነሳ ከሦስት ወለል በላይ ሊፍት የሚጠቀሙ ኮንስትክራሽን ሥራዎች አክርዲትድ በተደረገ ተቋም እንዲገነቡ ይፈለጋል፤ ግን ይህም አስገዳጅ አይደለም፡፡ ይሁንና በየዓመቱ በዚህ ዘርፍ የምንከፍለው ዋጋ ይታወቃል፡፡ በተሽከርካሪ አደጋ የሚጠፋው የሰው ሕይወት እና ንብረት ውድመት ይታወቃል፡፡ ቢያንስ መንግስት ጨረታዎችን ሲያወጣ አክርዲት የተደረጉ ተቋማት ግድ ነው የሚለው ባይገባበትም እንኳን፤ አክሪዲት የሆነ ተቋም ቅድሚያ ይሰጠዋል የሚለው ሐሳብ ቢያካትት የተሻለ ነው፡፡ አሁን ላይ ችግሮቹን ለመፍታት ከኮንስትራክሽን እና ከትራንስፖርት ሚኒስቴር ጋር ሥራዎችን እየሰራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡-በውጪዊ አሰሰሮች አክሪዲትድ የማድረግ ሂደቱ ለሙስና የመጋለጥ ዕድል የለውም?**

**አቶ ወንድወሰን፡-** አለው፤ ግን ጠባብ ነው። ለብልሹ አሰራርና ሙስና የመጋለጥ ዕድሉ በሁሉም የመንግስት አገልግሎቶች ላይ ሊኖር ይችላል፡፡ መነጋገር ካለብን ለሙስና የመጋለጥ ደረጃው ላይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የመጋለጥ ዕድል አለው፡፡ ግን በላብራቶሪ ስለሚረጋገጥ በጥቂቶች ይሁንታ ብቻ የሚሆን አይደለም፡፡

ከላብራቶሪ ሥራ በተጨማሪም በቡድን የሚሠራ በመሆኑ ለሙስና የመጋለጥ ዕድሉ ጠባብ ነው፡፡ ሙስና የሚስፋፋው ውሳኔ ሰጪነት በአንድ ወይንም ሁለት ግለሰብ እጅ ብቻ ሲሆን ነው፡፡ ነገር ግን ውሳኔ በቡድን ሲሆን ሙስና በጣም ይቀንሳል፡፡ በመሆኑም ከደንበኛ ጋር በመሆን ወይንም በመመሳጠር የሚፈፀም ሙስና አይኖርም ወይንም ለሙስና ተጋላጭነት ዕድሉ በጣም ጠባብ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ማግኘት የሚፈልጉ በርካታ አገልግሎት ፈላጊዎች እንደሚጉላሉ በተደጋጋሚ ይናገራሉ፡፡ ይህ ከሙስና ጋር አይያያዝም?**

**አቶ ወንድወሰን፡-** ይህ በዚህ ደረጃ አሳሳቢ አይመስለኝም፡፡ እንደ ሀገር ብሔራዊ የጥራት መሠረተ ልማት ‹‹National quality infrastructure›› አለ። የጥራት ተቋም የምንላቸው አሉ፡፡ እነዚህ የጥራት ተቋማት የእኛ ብቻ አይደሉም፡፡ ለአብነት የኢትዮጵያ ደረጃዎች ምደባ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት አሉ፡፡

የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የእኛ ደንበኞች ናቸው። የአንድ ነገር ትክክለኛነት ወይንም ልክነት በራሱ



**አክሪዲቴሽን አገልግሎት የትውልዱ የሕልውና ጉዳይ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከመኖር የሚቀድም ዓላማ የለውም። አክርዲቴሽን አገልግሎት ደግሞ ከሕይወታችን ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው፡፡ የጥራት ጉዳይ በጣም አንገብጋቢ አጀንዳችን ነው**

መስፈሪያ ወይንም አሰራር የሚያረጋግጠው የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ነው፡፡ ሥነ-ልክ የአንድን ነገር ልክ ልኩን የመለካት አቅምና ብቃት አለው ወይ የሚለውን ደግሞ እኛ አክሪዲት እናደርጋለን፡፡

የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት በተመሳሳይ ብቃቱንና አቅሙን መልኩ እኛ አክሪዲት እናደርጋለን። ሆኖም ሀገር ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች አክርዲት ለመደረግ አስገዳጅ ባለመሆኑ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። እንደ ሀገር ግን የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት አስፈላጊነት አስገዳጅ ባለመሆኑ በዚህ ግንዛቤ የመፍጠርና ማስፋት ላይ እየሰራን ነው፡፡ እኔ እስከማውቃው ድረስ ለሙስና የተጋለጠ ወይንም ይህን በተመለከተ የቀረበ አቤቱታ የለም ፡፡ ነገር ግን የደንበኞችን ጥያቄ በፍጥነት ያለመመለስ ወይንም መዘግየት ሊኖር ይችላል፡፡ እዚህ ላይ ሌብነት ሙሉ ለሙሉ ዝግ ነው እያልኩ አይደለም፡፡ እንደ ሀገር ሙስና ተብትቦ ሊጥለን ስለመሆኑ በተደጋጋሚ የተነገረ በመሆኑ ነባራዊ ሁኔታዎችን መደበቅ አይቻልም።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የባህር በር ወይንም የወደብ ባለቤት ለመሆን የሚያስችላት የመግባቢያ ውል አስራለች፡፡ ይህ ደግሞ በገቢ እና ወጪ ምርቶች ላይ ከተለመደው አሰራር የተለየ ሲሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት በዚህ ደረጃ ምን ያህል ዝግጁ ነው?**

**አቶ ወንድወሰን፡-** ልክ ነው፡፡ የባህር በር ወይንም የወደብ አገልግሎት በአጠቃላይ ንግድ ነው። እኛ በዚህ ሴክተር ውስጥ ነን፡፡ ይህ ወደብ የመጣው ለእኛ ነው፡፡ ስለዚህ ከየትኛውም ሴክተር በላይ ሥራ ይበዛብናል፤ ጥርጥር የለውም፡፡ ዓለም አቀፍ ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ ለመሆን የወደብ መገኘት ብቻ ሳይሆን ሰዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው እየሰራን ነው። አሁን ባለው ዓለምአቀፋዊነት እሳቤ ውስጥ መሪ ተዋናይ ለመሆን እየሰራን ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ከኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ምስክርነት የሚፈልግ ማህበረሰብ እየተበራከተ ይሄዳል፤ በዚህም ሥራ እየበዛ ይሄዳል፡፡

ቀደም ሲል በሰው ወደብ እና በአንድ መንገድ ስንሯሯጥ እና ምርቶችን ወደ ውጭ ስንልክ ነበር፡፡ ነገር ግን በራሳችን ወደብ ምርትና አገልግሎቶችን መላክ ስንጀምር ፍሰቱ አሁን ካለው መጠን ይጨምራል፡፡ ምርት ወደ ውጭ የሚልኩ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተቋማትም ይበራከታሉ፡፡

የውጭ ባለሃብቶችም ኢትዮጵያን ለኢንቨስትመንት መዳረሻነት እንደሚመርጧት ይታወቃል፡፡ አሁን ያለን ሠራተኛ መኖር ከሚገባው አንድ አራተኛው ነው፡፡ ካለን ሰራተኞች በእጥፍ የሚበልጠው ‹‹የፓር ታይም›› ሠራተኞች ናቸው፡፡ በመሆኑም አሁን ካለው ሰራተኛ በአራት እጥፍ መቅጠር ይጠበቅብናል፡፡

ስለዚህ ከወደቡ ባለቤትነት ጋር ተያይዞ አሁን ባለን አቅም ብቻ ብዙ መራመድ እንደማንችል እናውቃለን። ሕንፃ ግንባታችን በፍጥነት አጠናቀን በበቂ የሰው ኃይል ወደ ሥራ ለመግባት ጥድፊያ ላይ ነን፡፡ በወደቡ ዓማካይነት ወደ ውጭ ለምንልካቸውና ወደ ሀገር ውስጥ ለምናስገባቸው የግብርና፣ ኢንዱስትሪ ምርቶች እና አገልግሎቶች በፍጥነትና በጥራት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አሰራር እንፈጥራለን፡፡

ከዚህ በሻገር የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ላለፉት 13 ዓመታት በርካታ ልምዶችን አካብቷል። ከአፍሪካ የላብራቶሪ ትብብር እና ዓለም አቀፍ የላብራቶሪዎች ትብብር ጋርም ያለው ወዳጅነት በጣም ጤናማ ነው፡፡ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራትም በመምጣት ከኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ልምድ እና ተሞክሮ የሚቀስሙ አሉ፡፡ ሌላው ቀርቶ የሕንድ ትልልቅ ድርጅቶች የአክርዲቴሽን አገልግሎት እንድንሰጣቸው ሥምምነት ፈጽመናል፡፡

የሶማሌላንድ ጋርም በተመሳሳይ የአክሪዲቴሽን ሥምምነት ለመስጠት እየሰራን ነው፡፡ ከበርካታ የአፍሪካ ሀገራት ጋር ደግሞ የአክርዲቴሽን የሥራ ግንኙነት አለን፡፡ አቅማችንም እያደገ ነው፡፡ አንዳንዶች ችግር እየገጠማቸው ነው፡፡ ለአብነትም ኬኒያ በተለያዩ ወሰኖች አግኝታ ከነበረው እውቅና የተወሰዱባት ወሰኖች አሉ፡፡

ኢትዮጵያ ግን መሰል ችግሮች አላጋጠሟትም። ይልቁንም በየዓመቱ አዳዲስ የዕውቅና ወሰኖችን እየጨመርን ነው፡፡ ባለሙያዎቻችንም በአክሪዲቴሽን አገልግሎት ዙሪያ መለስ ማዕቀፍ ውስጥ በደንብ እየሄዱ ነው፤ ልምድም በሰፊው በማካበት ላይ ናቸው። ይሁንና አክሪዲቴሽን አገልግሎት እንደ ሀገር በሕዝቡ እና በመንግስት ሥራ ኃላፊዎች በሚገባው ልክ አልተሰራበትም፡፡ የመገናኛ ብዙሃን በዚህ ላይ ትልቅ ሚና እንዳላቸው እናምናለን፡፡

አክሪዲቴሽን አገልግሎት የትውልዱ የሕልውና ጉዳይ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከመኖር የሚቀድም ዓላማ የለውም፡፡ አክርዲቴሽን አገልግሎት ደግሞ ከሕይወታችን ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው፡፡ የጥራት ጉዳይ በጣም አንገብጋቢ አጀንዳችን ነው፡፡ ሕብረተሰባችን አሁን ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ በተቃራኒ ለጥራት የተሻለ ማሕበረሰባዊ ዕይታ አለው፡፡ እኛም ከብዛት ጥራት የሚል ብሂል በተግባር እስከምናረጋግጥ ድረስ እንሰራለን፡፡ በብዙ የማሕበረሰባችን ክፍልም ጥራት ይወደዳል፤ ይፈለጋል፤ ይፈቀዳልም፡፡

ነገር ግን ወደ ንግድ በምንገባበት ጊዜ ጥራት የሌለው ነገር አግበስብሶ ተገቢ ባልሆነ መንገድ የመክበር ዝንባሌ ያላቸው አንዳንድ ነጋዴዎች አሉ። እነዚህ ነጋዴዎች ለጥራት የሚሰጡት ትኩረት እምብዛም አይደለም። ሆኖም የማሕበረሰቡን አመለካከትና ግንዛቤ መቀየር ከተቻለ፤ አዋጅና መመሪያዎች ባያስገድዱም ሕብረተሰቡ ማስገደድ ይጀምራል የሚል እምነት አለን።

በመሰረቱ የትኛውም ዓለም ላይ አክርዲቴሽን አገልግሎት አስገዳጅ አይደለም፡፡ ማስገደድ የሚቻለው ግንዛቤ በመፍጠር ነው፡፡ በመሆኑም በሀገራችን በተለያዩ ዘርፎች ላይ ብቃት አለን ብለው እውቅና የሚሰጡ አካላት ወይንም ድርጅቶች ብቁ ናቸው ብለው እውቅና ከመስጠታቸው በፊት በራሳቸውም ብቃት እንዲኖራቸው ጭምር መሥራት ይገባል፡፡ እንደ አጠቃላይ ዓለም አቀፍ ሳይንሱን ስንመለከተው እኛ ከነካናቸው ዓለም አቀፍ ወሰኖች ይልቅ ያልነካናቸው በጣም ብዙ ናቸው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት ክንደ ብርቱ ነው ለማለት ከ10 ስትራቴጂክ እቅዱ በመነሳት የት እንጠብቀው?**

**አቶ ወንድወሰን፡-** 2022 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን አገልግሎት በአፍሪካ የአክሪዲቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ ግንባር ቀደም ለመሆን አቅደን እየሰራን ነው፡፡ አሁን ካሉን በላቀ ሁኔታ በሁሉም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው ወሰኖች ግንባር ቀደም ለመሆን እየተጋን ነው፡፡ ስለዚህ በ2022 ዓ.ም በአፍሪካ ብሎም በዓለም አቀፍ ዕውቅና ቀዳሚ እንሆናለን። በተመሳሳይ የማሕበረሰባችን፣ ምርት ላኪዎችና አስመጪዎች እና ሌሎች አገልግሎት ፈላጊዎች የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና የላቀ ምዕራፍ ላይ እንዲገኙ እንተጋለን፤ ግባችንን ለማሳካትም ያለመታከት እንሰራለን፡፡

**አዲስ ዘመን:- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ሳደረጉት ቆይታ አመሰግናለሁ::**

**አቶ ወንድወሰን፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ክልሉ በተፈጥሮ ማዳበሪያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ሲሆን፤ በዚህም በተያዘው በጀት ዓመት ማዳበሪያን በመጠቀም ሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት ወጥኗል።

እንደ ዳይሬክተሩ ንግግር፤ ክልላቸው መሬቱን የሚያለማው የተፈጥሮ ማዳበሪያን በመጠቀም ሲሆን ይህም በሶስት የተለያዩ መንገዶች አማካኝነት የሚከወን ይሆናል።

በዳይሬክተሩ ማብራሪያ መሠረት፤ የተፈጥሮ ማዳበሪያው በትል፣ ባዮጋዝና መደበኛ የኮምፖስት ዝግጅት አካሄድን በመጠቀም የሚሠራ ነው።

አቶ እሸቱ በንግግራቸው፤ ትልን በመጠቀም የተፈጥሮ ማዳበሪያ የማምረት ሂደት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጀመረና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣት የቻለ ነው።

ከዚህ ቀደም በዓመት 200 ሺህ ኩንታል የሚመረት ሲሆን በአሁኑ ወቅትም 2 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል የትል ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ፣ እስካሁን 1 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል ለማዘጋጀት ተችሏል።

አቶ እሸቱ 938 ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ በ265 ወረዳዎች የትል መራቢያ ማዕከላት ግንባታ እየተከወነ መሆኑን እንዲሁም በሚቀጥለው ዓመት ደግሞ ማዕከላቱ በሁሉም ቀበሌዎች ውስጥ የሚገነቡ መሆኑን ጠቅሰዋል።

አቶ እሸቱ የትል ማዳበሪያን ለማምረት የኦሮሚያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ድጋፍ እያደረገ መሆኑን በመግለፅ ይህን ዘዴ ተጠቅመው ገበሬዎች ማዳበሪያን አምርተው በመሸጥ ላይ ናቸው ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ ባዮ ጋዝን በመጠቀምም 270 ሺህ በላይ ኩንታል የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለማዘጋጀት ታቅዶ እስካሁን ድረስም 282 ሺህ የሚጠጋ ኩንታል ማዘጋጀት የተቻለበት ሁኔታ አለ ብለዋል።

በሁሉም ወረዳዎች ሞዴል የኮምፖስት ማቀነባበሪያ ማዕከላት የተዘጋጁ ሲሆን፤ በዚህ ዓመት 150 ሚሊዮን ኪዩቢክ ሜትር መደበኛ ኮምፖስት ለማዘጋጀት ታቅዶ እስካሁን 120 ሚሊዮን ኪዩቢክ ሜትር የሚጠጋ ተዘጋጅቷል።

የኬሚካል ማዳበሪያ አለምአቀፋዊ ዋጋ መጨመሩን ተከትሎ የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀም ሀገሪቷ ማዳበሪያ ግዢ የምታወጣውን በርካታ የውጭ ምንዛሪ ወጪ መታደግ የሚችል ስለመሆኑም አቶ እሸቱ ገልጸዋል።

በዳይሬክተሩ ንግግር መሠረት፤ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ጠቀሜታ በርካታ ሲሆን ከነዚህ ውስጥም የአካባቢ ጥበቃ፣ የአፈር መሸርሸርን መቀነስ፣ አፈር ውሃን እንዲይዝ በማድረግ የአፈር እርጥበትን መጨመር፣ የአፈር አሲዳማነትን መቀነስ ይገኙበታል።

# በደምበል ሐይቅ የሚከናወነው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የማስታወቂያ ሥራዎች ተሠርተዋል ብለዋል።

የጥምቀት በዓል የባቱ ከተማን የቱሪዝም ማዕከል የሚያደርግ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዓሉ የከተማው የገቢ ምንጭ በመሆኑ የቱሪዝም አቅምን በማሳደግ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ነው ብለዋል።

ባቱ የቱሪዝም መዳረሻ እና ሕዝቦች ተቻችለው የሚኖሩባት ከተማ መሆኗን ይበልጥ ማስተዋወቅ ይገባል ያሉት ከንቲባው፤ የጥምቀት በዓልን ለቱሪዝም ገቢ ማሳደጊያነት ከመጠቀም ባለፈ የመቻቻልና የአብሮነት ማሳያ የሆነውን ትርዒት በድምቀት ለማክበር አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉን አስረድተዋል።

የጥምቀት በዓል በድምቀት ከሚከበርባቸው የሀገሪቱ ከተሞች መካከል የባቱ ከተማ አንዷ መሆኗን የገለጹት ከንቲባው፤ ከአካባቢው ሕዝብ ጋር በመተባበር በዓሉን በሰላማዊና በደመቀ ሁኔታ ለማክበር ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

በዓሉ የሚከበርበትን አካባቢዎች በማጽዳትና በማዘጋጀት በዓሉን በጋራ ለማክበር የሚያስችል ዝግጅት መደረጉን ተናግረው፤ በከተማዋ የተቋቋመው የበዓሉ አከባበር ዐቢይ ኮሚቴ በእንግዶች አቀባበል፣ በመስተንግዶና ሆቴሎች እንዲሁም በሰላምና ጸጥታ ጉዳዮች አስፈላጊው ቅንጅታዊ ሥራ እያከናወነ መሆኑን አስታውቀዋል።

እንደ ክልል የጥምቀት በዓል በባቱ ከተማ በድምቀት ይከበራል ያሉት ከንቲባው፤ በርካታ ቁጥር ያላቸው የከተማው ነዋሪዎች፣ የሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ የሚገኙ ታዳሚዎች የሚሳተፉበት በዓል በመሆኑ ኃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ ይከበራል ብለዋል።

የከተማ አስተዳደሩ ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሚመጡ ታዳሚዎች ተገቢውን አቀባበል ለማድረግ ዝግጅት መደረጉንም ከንቲባው አመላክተዋል።

ዘንድሮ በዓሉን በተመለከተ በተሠራው ሰፊ የማስተዋወቅ ሥራ ካለፉት ዓመታት የተሻለ የጎብኚዎች ቁጥር እንደሚኖር ይገመታል ሲሉ ተናግረዋል።

በዓሉን ለማክበር የሚመጡ እንግዶች ላይ ምንም አይነት የዋጋ ጭማሪዎች እንደማይኖር ከአገልግሎት ሰጪችና ነጋዴዎች ጋር ምክክር መደረጉን ጠቁመው፤ በዓሉ በተሻለ መግባባትና የደስታ ስሜት እንዲጠናቀቅ ያላቸውን ምኞት ገልጸዋል።

# «ኢትዮጵያ በቀጣናው

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መንግሥት መቋቋምና ሀገር መምራት የቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ የኢትዮጵያን ባለውለታነት የሚያሳይ ነው።

ኢትዮጵያ ይህን ሁሉ ስታደርግ ለከፈለችው መስዋዕትነት የሚመጥን ተጠቃሚነት ግን አልነበረም ብለዋል አምባሳደር ፍጹም። ለአብነትም ሞቃዲሾ ውስጥ ተነጻጻሪ ሠላም እንዲመጣ ያደረገችው ኢትዮጵያ ብትሆንም ከሞቃዲሾ ተጠቃሚ የሆኑት ግን ሌሎች ሀገራት መሆናቸውን አንስተዋል።

ቀጣናው ላይ ኢትዮጵያ የምታደርገውን ያህል አስተዋጽኦ የሚመጥን ተጠቃሚነት ሊኖር እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ይህንን ደግሞ በድርድር፣ በሰጥቶ መቀበል መርህ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ገልጸዋል።

አምባሳደር ፍጹም፤ "ሰጥቶ መቀበል በሚባለው መርህ ስንሰጥ እንጂ ሰንቀበል አልኖርንም፤ አሁንም በቀጣይ የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መንገድ መሄድ አለብን። ስንሰጥ የቆየነው ለራሳችን ደህንነትም ካለን ስጋት ተነስተን ነው። የሶማሊያ ደህንነት እንዲጠበቅ ስንሠራ ቆይተናል። ይህንን የሚመጥን ድጋፍ ማግኘት እንድንችል ቁልፍ የሆነውን የዲፕሎማሲ ሥራ ማጠናከር አለብን" ሲሉ ተናግረዋል።

የጋራ ተጠቃሚነትን ማዕከል ያደረገ እንቅስቃሴያችን ማንንም የሚጎዳ ባለመሆኑ ስሜታዊ የሆኑ አካላት ሰከን ብለው ማሰብ እንደሚኖርባቸውም አስታውቀዋል።

አምባሳደሩ አክለውም፤ ኢትዮጵያ ከዓለም ጋር ተወዳድራ የምታመርታቸውን ምርቶች የተሻለ ተመራጭ መሆን እንዲችል በሀገር ውስጥ ያለው ተወዳዳሪ ሁኔታዎች መፈጠር እንዳለባቸው፤ በቴክኖሎጂ የታገዘ የኦን ላይን ሲስተሙ የተጠናከረ መሆን እንዳለበት፤ የባቡር መስመሩን ጨምሮ መሠረተ ልማቱ መስፋፋት እንዳለበትና፣ ዋጋቸውም ርካሽ መሆን እንዳለባቸውና የማይቆራረጥ ኤሌክትሪክ መቅረብ እንዳለበት ገልጸዋል።

ኢንቨስተሩና ሌላውም ባለድርሻ አካል ፈጣን በሆነና በአነስተኛ ዋጋ ምርት ለዓለም ገበያ ማቅረብ ቢችል ብዙ መወዳደሪያ አቅሞች እንደሚፈጠሩ ጠቅሰዋል።

ከተለያዩ ቦታ የሚመጡ ኢንቨስተሮችና ባለሀብቶች ብዙ ቦታ ላይ ልምድ ያላቸው በማለት፤ ከሌሎች ወደቦች ዋጋ ጋር አወዳድረው አሁን የሚጠቀሙበት ዋጋ ውድ እንደሆነ፣ አፈጻጸሙም ቀልጣፋ እንዳልሆነ በማመን ይህ ቅናሽ ሊደረግበት እንደሚገባና ቀልጣፋ መሆን እንዳለበት አስተያየቶችን እንደሚያቀርቡ ተናግረዋል። ፋብሪካዎች የሚገኙባቸው ቦታዎች ከወደብ የራቁ በመሆናቸው የየብስ ትራንስፖርቱን ዋጋ ከዓለም ጋር ሲወዳደር ውድ እንደሆነ ቅሬታዎች እንደሚነሱ ጠቁመው፤ የባህር በሩ ሲሳካ እነዚህ ችግሮች እንደሚቀረፉ ገልጸዋል።

# ትርክቶች የፈተኑት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቅፋ የኖረች ሀገር መሆኗ ኢትዮጵያውያን ሁለንተናቸው በአብሮነት፣ በአንድነትና በህብረት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማስቻሉን ይናገራሉ።

በገጠርም ሆነ በከተማ ኢትዮጵያውያን አኗኗራችንና አሠራራችን ማህበራዊ ነው የሚሉት መጋቢ ምስጢር አእመረ፤ በተለይ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ገበሬዎች የሚያርሱት፣ የሚያርሙትና የሚያጭዱት በደቦ ነው። ለቅሶ ኀዘናችን፣ ደስታ ሰርጋችን አብሮነት ያለው ማህበራዊ ነው። በአጠቃላይ ሁሉ ነገራችን በአብሮነት የሚከናወን ነው። ይሄ አብሮነት የሥነልቦና ጥንካሬን የሚሰጥ ኃይል ነው ይላሉ።

አክለውም፤ ሃይማኖታዊ መጽሐፍት ሰው ብቻውን ወደ ሥራ ሊሰማራ አይገባም፤ እንቅፋት ቢመታው፣ አይኑ ላይ ግድፍ ቢገባበት እንኳን ሊረዳው የሚችል ሰው ያስፈልገዋል እንደሚሉ አመላክተው፤ አብሮነት በሃይማኖትም ሆነ በባህል ዓይን ከኢትዮጵያውያን ጋር የተቆራኘ ኃይላችንና መድመቂያችን እንዲሁም በሌላው ዓለም የምንታወቅበት ከአባቶቻችን የተቀበልነው መለያ ትውፊታችንና እሴታችን ነው ብለዋል።

"ጣሊያንን የመለሰው የአንድ አካባቢ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም። ከአራቱም ማዕዘን የኢትዮጵያ ክፍል እያንዳንዱ አውራጃ የሚችለውን ያህል ሠራዊት እየያዘ ወደ ዓድዋ ተምሟል" ሲሉም ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው ላይ የጠላት እጆች ሲቀሰሩ በህብረትና በአንድነት ጠላታቸውን ወደ ኋላ የሚመልሱ ሕዝቦች መሆናቸውን ያወሳሉ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ የኢትዮጵያውያን መለያ የሆነው እሴት አንዳንድ ወገኖች በሚፈጽሟቸው ተግባራት እየተሸረሸረ መጥቷል የሚሉት መጋቢ ምስጢር አእመረ፤ አባቶቻችን በአብሮነት ምን አይነት ታሪክ አስመዘገቡ የሚለውን ወደኋላ መለስ ብለን ማስታወስ ይገባናል። በአንጻሩ በምዕራቡ ዓለም የነገሰው ግለኝነት ቀልብ ያለውን ማህበረሰብ አፈራርሶና ነጣጥሎ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶቻችንን ምን ያህል እንደሸረሸረ በመወየየት ዘመናዊነት አድርገን እየተቀበልን ያለነው ሃሳብ ከነበርንበት ማማ እያወረደን እንጂ ከፍ እያደረገን እንዳልመጣ ለትውልዱ ማስተማር ይኖርብናል ሲሉ ይመክራሉ።

አያይዘውም፣ ግብረገብ የሆነ ትውልድ ለመቅረጽ ወርቃማ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶቻችንን ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በማካተት ጎልተው እንዲወጡ ማድረግ ያስፈልጋል። በአጠቃላይ መንግሥት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሀገር ሽማግሌዎች አብሮነትና አንድነት ይበልጥ እንዲጎለብት በየፊናቸው ኃላፊነታቸውን መወጣት ከቻሉ የቀደመ ቁመናችን ላይ ለመገኘት እንችላለን በማለት የተናበበና ጠንካራ ሥራ እንደሚጠበቅ ይጠቁማሉ።

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ልዩ አማካሪ ኡስታዝ አቡበከር አህመድ በበኩላቸው ኢትዮጵያውያን ላለን አብሮነትና አንድነት መነሻ የሚሆነው ታሪካችን ነው። በታሪክ አጋጣሚ ሁሉም እምነቶች በሚባል ደረጃ የእስልምና፣ ክርስትና እና አይሁድ እምነቶች ከመካከለኛው ምስራቅ ነው ወደ ሀገራችን የገቡት። እነዚህ ሃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ከመነሻው ኢትዮጵያ ለእምነት ነጻነትና መከበር እውቅናን የመስጠት መሠረት ያላት ናት ይላሉ።

በእስልምና ሃይማኖት ቅዱሳን አስተምህሮታችንና በነብያዊ ትንቢት ኢትዮጵያ የእውነትና የፍትህ ምድር ተብላ የተገለጸች ሀገር ናት። እምነትን መሠረት በማድረግ በታማኝነትና በእውነተኝነት የሚኖርባት የትናንት የአብሮነት ማንነት ያላት ሀገር ናት ሲሉም ያክላሉ።

ኢትዮጵያውያን በዘመናት ውስጥ እንደ ሀገር በተፈተንባቸው የጋራ ችግሮቻችን ወቅት የውስጥ ችግሮቻችንን በማቆየት አብሮነትን በማጠንከር የጋራ ጠላትን የመከትንበትን የከፍታና የልዕልና ታሪክ ማስመዝገብ የቻለ አንድነት ያለን ሕዝቦች ነን የሚሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ "በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደ ሀገር እየተጋፈጥናቸው ባሉ ፈተናዎች ምክንያት የትናንቱ ማንነታችንና አብሮነታችን በብዙ መልኩ ተሸርሽሮ ለአደጋ ተጋልጧል" ይላሉ።

በትናንት ማንነታችን ላይ ብቻ ተቀምጠን መኖር ስለማንችል ዛሬ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት እያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት እንዳለበት በተለይም ኢትዮጵያ የሃይማኖተኞች ሀገር በመሆኗ ትልቅ ድርሻ ያላቸው ቤተ እምነቶች መሆናቸውን ጠቁመው፤ "በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ቤተ እምነቶች ውስጥ የሚስተዋሉ ከሃይማኖት መሠረት ያፈነገጡ መንፈሳዊ ልዕልና የማይታይባቸው አግባብነት የሌላቸው አንዳንድ ሃሳቦች አሉ" በማለት እንዲህ ያሉ ሃሳቦች በተለያዩ ጊዜያት ብቅ እልም ማለታቸው እጅግ አደገኛ አዝማሚያ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

"የብዙኃን የመንፈስ እርካታ፣ የሰላምና የተስፋ ማግኛ ምንጮች የሆኑ ተቋማት ስለ ሰላም፣ አንድነት፣ ክብርና ፍቅር እንጂ ስለመለያየትና ስለመበታተን ማሰብ የለባቸውም" የሚሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ ይሄ ማለት ችግሮችን አይናገሩ፤ የጠፉ ነገሮች እንዲታረሙ አይሞክሩ ማለት አለመሆኑን አስታውሰው፣ ከሃይማኖት አባቶች ምክር መስጠት፣ መሸምገልና ማስታረቅ እንደሚጠበቅ ጠቅሰዋል፣ ይሄን ሲያደርጉ አብሮነትን ያስጠብቃሉ አንድነትን ያጸናሉ ሲሉም አክለዋል።

ምሁራን የሀገር ሽማግሌዎችም በታላላቆች ጥፋት ሲፈጸም ዝም ብሎ ተመልካችና የሆነ ቡድን ደጋፊ ሆነው ዳር ላይ መቆም እንደሌለባቸው ጠቁመው፤ "እኛን እየጎዳን የመጣው መሃል ላይ ያለው ሰው እያነሰ መምጣቱ ነው። መሀከል ላይ ሆኖ ሁሉንም በእኩል ዓይን አይቶ ተዉ ብሎ ስለሁሉም ችግር የሚጮህ፣ የሚያለቅስና መፍትሄ የሚፈልግ ሰው ያስፈልገናል" ብለዋል።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ቤተክርስቲያናት ህብረት ፕሬዚዳንት ፓስተር ጻድቁ አብዶ በሕዝቦች መካከል ችግር የለም ሲባል የፖለቲካ ቋንቋ አይደለም። ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ጥላቻ ቢኖረው ኖሮ የከፉ ተግባራት ሊፈጸሙ ይችሉ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮነት በብዙ መንገድ የሚገለጽ ነው ይላሉ።

በታሪካችን ቅያሜም ቢኖር ጠላት ሲመጣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት እንደሚቆም የሚታወቅ ነው። ኢትዮጵያውያን ብሄርና ቋንቋ ሳይለያቸው ተጋብተው ተዋልደው የሚኖሩ ናቸው የሚሉት ፓስተር ጻዲቁ፤ "ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአብሮነት የኖረውን ሕዝብ ለመለያየት የሚደረገውን ሙከራ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ላይ ቆሞ እምቢ ማለት አለበት" ሲሉ ያሳስባሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘመናት ውስጥ በችግርና በደስታ ዕኩል ተካፍሎ እዚህ መድረሱን ጠቅሰውም፤ በተለይ ከሃይማኖት አባቶችና ከሀገር ሽማግሌዎች የሚጠበቀው ማስታረቅ፣ መምከርና አለመወገን ነው። ፍቅርን፣ ምህረትንና ይቅርታን በመስበክ ሰው እርስ በእርሱ እንዲግባባ፣ እንዲታረቅና እንዲስማማ በማድረግ አብሮነት እንዲጠነክር መሥራት ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ይመክራሉ።

ምሁራንም ዜጎች እርስ በእርስ እንዲጠራጠሩ፤ አንዱ ሌላኛውን እንዲጠላ ከሚያደርግ መጥፎ አይነት ታሪክና ትርክት መራቅ አለባቸው። ሕዝብን የሚለያይ ክርክር ትተው አንድ የሚያደርጉትን እስከዛሬ በአብሮነት ያኖሩንን እሴቶች እያጠኑ ሕዝብ በሰላም በአብሮነት እንዲኖር መጣር ይገባቸዋል ሲሉ ጥሪ ያቀርባሉ።

ልዩነቶችን በማጉላትና የጸብ ምንጭ በማድረግ የሚፈጠሩ ግጭቶችና አለመግባባቶች መጠነ ሰፊ ጉዳት የሚያስከትሉ በመሆናቸው የተሻገረልንን የአብሮነት እሴት ጠብቀን ለቀጣዩ ትውልድ ልናሻግር ይገባል።

# የመጋዘን ደረሰኝ ብድር አገልግሎት- ለአርሶ አደሩ የፋይናንስ ተደራሽነት

ጽጌረዳ ጫንያለው

ግብርና በኢትዮጵያ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከተለያዩ የምጣኔ ሀብቱ ዘርፎች አኳያ ሲታይም እስከ 40 በመቶውን ድርሻ እንደሚይዝም መረጃዎች ይጠቁማሉ። በሥራ ዕድል ፈጠራም እንዲሁ እስከ 80 በመቶውን እንደሚሸፍን፣ በውጭ ምንዛሬ ግኝት በኩልም እንዲሁ ፋይዳው የጎላ ስለመሆኑ ይገለጻል፡፡

ይህ ግዙፍ ዘርፍ የሚገባውን ያህል በፋይናንስ እንዳልተደገፈ ይገለጻል፤ ይህንንም መንግስትን ጨምሮ የዘርፉ ምሁራንም በተደጋጋሚ ሲያስገነዝቡ ኖረዋል። መረጃዎች እንሚያመለክቱት፤ በ2014 ዓ.ም ባንኮች ለተለያዩ ዘርፎች ከሰጡት 427ነጥብ9 ቢሊዮን ብር አዲስ ብድር ውስጥ ለግብርናው ዘርፍ የተሰጠው ብድር 21ነጥብ4 ቢሊዮን ብር ብቻ ነው፡፡ ይህም የአጠቃላዩን የብድር ስርጭት አምስት በመቶ ድርሻ ይይዛል፡፡

ይህም ውጤት የተገኘው ቀደም ሲል በተደረጉ የአሰራር ማሻሻያዎች ምክንያት እንደሆነ ይታመናል፡፡ በተለይም በብሔራዊ ባንክ የወጣ በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚመሰረት ዋስትና ምዝገባ ጋር የተያያዘ መመሪያ ቁጥር MCR/01/2020 ባንኮች ከሚያበድሩት ገንዘብ ውስጥ ቢያንስ አምስት በመቶውን ለግብርናው ዘርፍ ብድር እንዲሰጡ በመደንገጉ እንደሆነ ይነሳል፡፡

በመሆኑም የግብርናውን ዘርፍ የፋይናንስ አካታችነት ለማረጋገጥ አዳዲስ አሰራሮችን መቀየስ የግድ ይላል። ከእነዚህ መካከል ደግሞ የመጋዘን ደረሰኝ ብድር አገልግሎት አንዱ ሲሆን፤ ይህም አርሶ አደሩን በስፋት ተጠቃሚ የሚያደርግ አሰራር እንደሆነ ይገለፃል፡፡

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የመጋዘን ደረሰኝ ብድር አገልግሎት ክፍል ስራ አስኪያጅ አቶ ብርሃኑ ጥሩነህ እንደሚሉት፤ እንደ ሀገር አርሶአደሩ ከምርት ሂደት አሳላጭነት ሚና ባለፈ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ መዋቅር እና የአሰራር ስርዓት በአግባቡ አልተበጀለትም። አርሶ አደሩ በዚህም በበጋ ፀሃይ እየተጉላላ ሞፈርና ቀንበር ተሸክሞ አርሶና አለስልሶ፤ በክረምት ዝናብ በብርድና ቆፈን ተኮራምቶ ዘርቶ፣ አርሞ፣ ኮትኩቶ፣ እያስራብ ምርቱን ቢሰበስብም፣ የልፋቱን ያህል ግን ተጠቃሚ አልሆነም፡፡

በአንፃሩ ደግሞ ነጋዴው ከገበሬው በርካሽ ገዝቶ በማቆየት የተሻለ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት አርሶአደሩ የራሱን ሕይወት በመቀየር ለተሻለ ኢንቨስትመንት የሚያበቃው ካፒታል ለመፍጠር ሳይችል ቆይቷል፡፡ አርሶአደሩን ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ በአሁኑ ወቅት መልካም ጅምሮች ይታያሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የግብርና ዘርፍ የፋይናንስ አካታችነት ሥራ ሲሆን፣ ይህም ትልቅ ሃገራዊ የፖሊሲ ኢኒሽቲቭ ነው፤ በዚህም ውስጥ የሚመለከታቸው ባለድርሻ ተቋማት በቅንጅት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

ከሥራዎቹ መካከል ደግሞ የመጋዘን ደረሰኝ ብድር አገልግሎት አንዱ መሆኑን አቶ ብርሃኑ ይጠቅሳሉ። ይህም ማለት ምርት ያለው አነስተኛ አርሶአደር፣ አልሚ ወይም ማህበራት ምርታቸውን በመጋዘን በማከማቸት፣ ላከማቹት ዕቃ ከባለመጋዘኑ ደረሰኝ በመቀበል፣ የመረከቢያ ደረሰኙኑን ደግሞ ለፋይናንስ ተቋማት በማቅረብ ብድር የሚገኙበት ስርዓት መሆኑን ያብራራሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት የመጋዘን ደረሰኝ የብድር ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተለዩት አካላት በአነስተኛ ማሳ የሚያመርቱ አርሶአደሮች፤ አልሚዎች እና የሕብረት ስራ ማሕበራት መሆናቸውን ያነሳሉ፡፡ እነዚህ አካላት ምርታቸውን ብቻ በማስያዝ በተመጣጣኝ ወለድ የብደር አገልግሎት ያገኛሉ ይላሉ፡፡ በዚህም በምርታቸው የላቀ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በተጨማሪም ደረጃውን በጠበቀ መጋዘን የክምችት አገልግሎት የሚያገኙ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ የዚህ ስርዓት መዘርጋት የድህረ-ምርት ብክነትን ይቀንሳል፤ የእሴት ሰንሰለቱ ስለሚያጥር የገበሬዎቹ ወጪ ያንሳል፤ በአንፃሩ ገቢያቸው ይጨምራል፡፡ በመሆኑም የተሻለ የኢኮኖሚ አቅም እንዲያገኙ በማስቻል የኑሮ ደረጃቸውን ከፍ እንዲያደርጉ ያግዛቸዋል፡፡

**ሰንሰለቱ አጭር፣ ወጭ ቆጣቢ፣ ግልፅና ተገማች እንዲሆን ያግዛል ሲሉ ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም አንደኛው የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ለሃገረ-መንግስት ግንባታው አዎንታዊ አስተዋፅዖን እንዳለው ይጠቅሳሉ፡፡ ከድህነት አዙሪት የተላቀቀችና የበለፀገች ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ አይነተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን ያብራራሉ**



የግብርናው ዘርፍ የመጀመሪያው ተዋናይ የሆነው አርሶአደር እንደ ሀገር በግብይት ሂደቱ ላይ የመደራደር አቅም ያለው ወሳኝ ተሳትፎ የለውም፡፡ በዚህ ረገድ የመጋዘን ደረሰኝ ብድር ስርዓት እንደ ሀገርም በብዙ መልኩ ጥቅሙ የላቀ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ከአጭር ጊዜ አንጻር በዋናነት አራት ጥቅሞች እንዳሉት ያመለክታሉ። ‹‹አንደኛው የፋይናንስ አካታችነትን እና ተደራሽነትን በግብርናው ዘርፍ ላይ ማረጋገጥ ነው›› ይላሉ፡፡

እንደ እርሳቸው ገለፃ፤ ሁሉም በሚባል ደረጃ ምርቱን ወደ ገበያ የሚያወጣው በመኸር ወቅት ብቻ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የምርት አቅርቦት ከፍተኛ ይሆናል። በአንጻሩ ይህንን ከፍተኛ አቅርቦት ሊሸምት የሚችል ተመጣጣኝ ፍላጎት በተጠቃሚዎች ዘንድ ላይኖር ይችላል፡፡ አቅርቦት ከፍላጎት በላይ ይሆናል ማለት ነው። በዚህ ምክንያት በመኸር የምርት ዋጋ ከሌሎች ወቅቶች አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ ይሆንና አርሶ አደሩ ሳይጠቀም ይቀራል፡፡

በአጣዳፊ የገንዘብ ፍላጎቱ ምክንያት ሌላ የገንዘብ ምንጭ ስለማያገኝ ብዙ የለፋበትን ምርት በእርካሽ በመሸጡ ጥቅሙን ለሌላ አሳልፎ የሚሰጥበት አጋጣሚ ብዙ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡ ‹‹በመጋዘን ደረሰኝ ስርዓት ግን ይህ ሁሉ ችግሩ ይፈታል፡፡ ምክንያቱም ምርቱን በእርካሽ ዋጋ ከመሸጥ ተጠብቆ የተሻለ ዋጋ ሲያገኝ መሸጥ እንዲችል ያግዘዋል›› ይላሉ፡፡ የብድር ማዕቀፍ ስለሚዘጋጅለትም ትርፋማ የሚያደርገው መሆኑን ነው ያስረዱት፡፡

የድህረ-ምርት ብክነትን የሚቀንስ መሆኑ ሁለተኛው ጥቅሙ መሆኑን አመልክተው፤ በኢትዮጵያም ሆነ በአብዛኛው ታዳጊ ሀገራት ከሚመረተው በቆሎ እስከ 30 በመቶ የሚሆነው ለታለመለት ጥቅም ሳይውል በተለያዩ ምክንያቶች እንደሚባክን ጥናቶችን ዋቢ አድርገው ይጠቅሳሉ፡፡ በተለይም በፍሳሽ፣ አይጥና ነቀዝን በመሰሉ ተባዮች፣ በእርጥበት የሚበላሽበት ሁኔታ መኖሩን ያስረዳሉ፡፡ ይሁንና የመጋዘን ደረሰኝ አሰራር ስርዓት የሚካሄደው ደረጃውን በጠበቀ የመጋዘን መሰረተ-ልማት መሆኑን ጠቅሰው፣ በሰለጠነ የሰው ኃይል የሚመራና የተሻለ የምርት አስተዳደር ስርዓት የሚከተል መሆኑንም ተናግረዋል፤ ይህም ከድህረ-ምርት አያያዝ ጋር የተያያዙ ችግሮችን እንደሚቀንስ ነው ያስገነዘቡት፡፡

በሶስተኛ ደረጃም የጥራትን ፅንሰ-ሃሳብ በአጠቃላይ ማሕበረሰብ ዘንድ በስፋት ለማስረፅ ይጠቅማል ባይ ናቸው፡፡ ይህም የሚሆነው ለምሳሌ አንድ የሰብል ምርት በመጋዘን በማስቀመጥ ብድር ለማግኘት የሚፈልግ አርሶ አደር፣ በምርት ገበያው የመጋዘን አስተዳደር የሚጠየቀውን ቢያንስ ትንሹን የምርት ጥራት መስፈርት የሚያሟላ ምርት ሲያቀርብ እንደሆነ ያነሳሉ። ለዚህ አገልግሎት የሚውሉ ሁሉም ምርቶች ወጥ ውል ያላቸው ሲሆን፤ ይህንን ውል መሰረት ተደርጎ የጥራት ደረጃቸው ታውቆ ደረሰኝ ስለሚሰጣቸው ጥራት ምን ያህል ዋጋ እንዳለው እንዲረዱ የሚያስችል እንደሆነ ነው ያስረዱት።

የመጋዘን ደረሰኝ ስርዓት የምርቶቹን የእሴት ሰንሰለት ቀልጣፋነት እንዲሻሻል ማድረጉ አራተኛው ጥቅሙ እንደሆነ አመልክተው፣ ይህም ሰንሰለቱ አጭር፣ ወጭ ቆጣቢ፣ ግልፅና ተገማች እንዲሆን ያግዛል ሲሉ ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም አንደኛው የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ለሃገረ-መንግስት ግንባታው አዎንታዊ አስተዋፅዖን እንዳለው ይጠቅሳሉ፡፡ ከድህነት አዙሪት የተላቀቀችና የበለፀገች ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ አይነተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን ያብራራሉ፡፡

እንደ አቶ ብርሃኑ ማብራሪያ፤ የመጋዘን ደረሰኝ ብድር ስርዓት በሶስት ዋና ዋና ተዋናዮች መካከል የሚካሄድ የሶስትዮሽ ቅንጅታዊ አሰራር ውጤት ነው፡፡ እነዚህም የመጀመሪያዎቹ ምርት አስቀማጮች ማለትም በመጋዘን ሊከማች የሚችል ምርት በማቅረብ ብድር ተጠቃሚ አካላት ሲሆኑ ለምሳሌ አምራቾችና ሕብረት ሥራ ማህበራት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ሁለተኛ የፋይናንስ ተቋማት ሲሆኑ እነሱም ለአስቀማጮች ብድር አቅርቦትን ያካሂዳሉ፡፡

አሁን ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጋር ስምምነት ባላቸው ሰባት ባንኮች አማካይነት ብድሩ ይሰጣል፣ እነዚህ ባንኮች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ አባይ ባንክ፣ አዋሽ ባንክ፣ ሕብረት ባንክ፣ ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ፣ ኦሮሚያ ባንክ እና አማራ ባንክ ሲሆኑ፣ ሌሎች 10 ተጨማሪ ባንኮችም በስምምነት ሂደት ላይ ያሉ በመሆናቸው ዝግጅታቸውን ሲጨርሱ ወደ ስራ የሚገቡ መሆኑን ነው ያብራሩት፡

‹‹የብድር ሂደቱን ስንመለከት በመጀመሪያ የብድር ፍላጎት ያለው ገበሬ ወይም ሕብረት ስራ ማህበር ያለውን ምርት ለምርት ገበያው መጋዘን ያመጣል፣ ምርቱ ደረጃ ይወጣለታል፣ በመመዘን ክብደቱ ይለካል፣ ይራገፋል፣ ከዚያ የምርት መረከቢያ ደረሰኝ ለምርት አስቀማጩ ይሰጠዋል›› በማለት ሥራአስኪያጁ ይናገራሉ፡፡ በመቀጠል ብድር ፈላጊው ከምርት ገበያ የተሰጠውን የመጋዘን ደረሰኝ በመያዝ ከባንክ ብድር የሚጠይቅበት አግባብ መኖሩን አልያም ቀደም ብሎ ማመላከቻ ማቅረብና የብድር ሂደቱን በማስጀመር ሰነዶችን እያሟላ ቆይቶ የመጋዘን ደረሰኝ በመጨረሻ ለባንክ ማቅረብ የሚችል እንደሆነ ያነሳሉ፡፡

ባንኩ በተበዳሪው የቀረበለትን የመጋዘን ደረሰኝ በዋስትና እንዲያዝለት ለምርት ገበያው የማረጋገጫ ጥያቄ ለዚሁ በተዘጋጀው መተግበሪያ ስርዓት የሚልክ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ገበያውም ሰነዱ ላይ አስፈላጊውን ማጣራት ካካሄደ በኋላ ለባንኩ የዋስትና ጥያቄ ምላሽ የሚሰጠው መሆኑን ባንኩ የምርት ገበያውን ማረጋገጫ እንደደረሰው ብድሩን ለተበዳሪው የሚፈቅድበት አግባብ መኖሩን ነው ያብራሩት፡፡

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ ባንኮቹ የምርት ገበያውን የክፍያ ስርዓት በመቀላቀል እና ክፍያን በማስፈጸም አብረው እየሰሩ ያሉ የጋራ የመተግበሪያ ስርዓት ያላቸው ሲሆኑ፣ በተጨማሪም ከገበያው ጋር ለመስራት ፍላጎት በማሳየት፣ የመጋዘን ደረሰኝ ብድር አገልግሎት ስምምነት ያደረጉ እንዲሁም ተገቢውን ስልጠናውን የወሰዱ ባንኮች ናቸው፡፡ ባንኮች የብድር ዋስትና መያዥያ የሚጠቀሙት የመጋዘን ደረሰኙን ብቻ ነው፡፡ ሌላ ተጨማሪ መያዥያ አያስፈልግም፡፡

ብድር አመላለስን በተለመከተ በመጀመሪያ የተሻለ ዋጋ ሲያገኙ ጠብቀው ምርቱን በመሸጥ ብድሩን መመለስ ይችላሉ ይላሉ፡፡ ሌላ የገንዘብ ምንጭ ካገኙ ሳይሸጡ ብድሩን መመለስ ይችላሉ፤ ይህ ካልሆነ ባንኩ በመረከብ መሸጥ የሚችል ሲሆን፤ ከሸጠ በኋላ ትርፍ ገንዘብ ካለ ይህንን ገንዘብ ለተበዳሪዎች የሚመለስ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

ከአጭር ጊዜ አኳያ፣ የመጋዘን ደረሰኝ ብድር ስርዓት የተዛነፈውን የምርት ፍላጎትና አቅርቦት በመሻሻል፣ ዓመቱን ሙሉ የተመጣጠነ የምርት ፍሰት እንዲኖር የሚያግዝ መሆኑን ሥራአስኪያጁ አመልክተው፤ ይህም አላስፈላጊ የዋጋ መዋዠቆችን የሚያስቀር መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

በተጨማሪም የምርት መገኛ ግልፅነትን ስለሚፈጥር በተደራጀ የመረጃ ስርዓት የታገዘ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ያለውና በሃገሪቱ በአንዳንድ ነጋዴዎች ዘንድ የሚታየውን ምርትን የመደበቅና ሰው-ሰራሽ እጥረት በመፍጠር የምርት ዋጋን በማናር በአቋራጭ የመበልፀግ ስሁት ልምምድን የመግታት አቅምን ይፈጥራል ባይ ናቸው። ይህ ደግሞ የኑሮ ውድነትን ለመቀነስ እንደሚረዳ ጠቅሰው፤ በተጨማሪም የምርት እሴት ሰንሰለትንም ስለሚያሳጥር የመጨረሻ ተጠቃሚዎች በተሻለ ዋጋ ከአምራቾች ወይም ሕብረት ስራ ማህበራት በተመጣጣኝ ዋጋ የመግዛት እድልን የሚፈጥር መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ፤ ምርትና ምርማነት እንዲያድግ፣ ተጨማሪ ምርት እንዲመረት ያደርጋል፣ በምግብ እራስን የመቻል አቅምን። አርሶ አደሩ አጣዳፊ የገንዘብ ፍላጎቱን ለመቅረፍ ብዙ የለፋበትን ምርት በመኸር ወቅት በእርካሽ እንዳይሸጥ ያደርገዋል፡፡ የመጋዘን ደረሰኝ ብድር ስርዓትን እንደ አማራጭ በመጠቀም አቆይቶ በተሻለ ዋጋ የመሸጥ ልምድን እንዲያዳብር ያግዘዋል፡፡

ከምርቱ የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆንና ገቢውን ከፍ እንዲያደርግ፤ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂን በተደራጀ አልያም በተናጠል እንዲጠቀም እድል ይፈጥርለታል። የተሻሻሉ ቴክኖሎጂን ሲጠቀም ደግሞ ሀገር ያላትን የተፈጥሮ ፀጋ ለምሳሌ የውሃ ሃብት በአግባቡ ይጠቀማል። በዚህም ምርታማነት ይሻሻል፣ በዝቅተኛ የማምረቻ ወጭ ተጨማሪ ምርት ይፈጠራል፤ በዚህም ለሃገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ፣ ለፋብሪካዎች ጥሬ ዕቃነት የሚውል በቂ ምርት እንዲያቀርብ ይረዳዋል፡፡ ይህ ደግሞ ከእጅ ወዳፍ ኑሮ በመውጣት የተሻለ ቁጠባ ያካሂዳል፡፡

ከረዥም ጊዜ አኳያ ደግሞ የግብርና ፋይናንስ አካታችነት የፖሊሲ ኢኒሼቲቭን በአግባቡ በመተግበር የዘርፍ ሽግግርን በፍጥነትና ዘላቂ በሆነ መንገድ በማሳለጥ አብዛኛው ዜጎቿ ከድህነት የተላቀቁባትና የበለፀገች ኢትዮጵያን ሀገረ-መንግስት ዕውን ለማድረግ እንደሚረዳም ነው ያብራሩት፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ሁሉም ባህሎቻችን የሁላችንም ናቸው

**ዋለልኝ አየለ**

የፊታችን ቅዳሜ ጥምቀት ነው፡፡ በጃን ሜዳ ኢትዮጵያን እናያለን፡፡ እርግጥ ነው በዓሉ ሃይማኖታዊ ነው፡፡ በጃን ሜዳ የሚታየው ግን ሁለቱም ነው፡፡ ከትሪቡኑ ጊቢ የዲያቆናትና ካህናት ዝማሬዎችና ሌሎች ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ይከወናሉ፡፡

ጃን ሜዳ ከመግቢያ በሮች ጀምሮ ሙሉ ሜዳው ግን በባህላዊ ጨዋታዎች ይደምቃል፡፡ ወደ ጃን ሜዳ በሚወስዱ መንገዶችም እንደዚያው። እነዚህ ጨዋታዎች በመላው ሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የሚከወኑ ናቸው፡፡

አንዳንድ ፖለቲከኞቻችን የመከፋፈልና የመነጣጠል ሥራ ለመሥራት ከፋፋይ ንግግሮች ሲያደርጉ ስንሰማ ኖረናል፡፡ ከአንዲት ሀገር ውስጥ «ይሄ የአንተ አይደለም፤ ይሄ አይመለከትህም፤ ይሄን አታድርግ!» ሲሉ ይታያል፡፡ ይባስ ብሎም አንዱ ብሄር በሌላው ላይ የጫነው ነው በማለት ጫኚና ተሸካሚ ያደርጉታል፡፡ የኢትዮጵያ መለያ ሆኖ የኖረ ምልክት ወይም ጌጥ «አይ! ይሄማ የእገሌ ብሄር ነው» በማለት የዚያ ብሄር ተወላጅ ያልሆኑ እንዲጠሉት ይደረጋል፡፡ ለመሆኑ የኢትዮጵያ ባህል የማነው? የአንድ ብሄር ነው ከተባለ የየትኛው ብሄር ነው? የዚህ ብሄር መለያ የሆነው ከመቼ ጀምሮ ነው? ከዚያ በፊት የማን ነበር?

እነዚህን ጥያቄዎች ስንጠይቅ መልሱ አንድ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የሁሉም ብሄር ነበር፡፡ የሆነ ወቅት ላይ ኦሮሞ ውስጥ ይታይ የነበረው በሂደት አማራ ወይም ትግራይ ውስጥ ይገኛል፡፡ አማራ ወይም ትግራይ ውስጥ የነበረው ከሆነ ዘመን በኋላ ኦሮሞ ወይም ሶማሌ ውስጥ ይገኛል። በቀደመው ዘመን የነበሩ ወታደራዊ ዘመቻዎች ይህን ለማድረግ ያስገድዳሉ፡፡

ደራሲ በዕውቀቱ ሥዩም ከተናገረው አንድ ገጠመኝ ልነሳና ወደ ዋናው ትዝብት ልግባ፡፡ በዕውቀቱ ጎጃም ውስጥ ነው ተወልዶ ያደገው፡፡ ጎጃም አማራ ነው። እናም እሱ ባደገበት አካባቢ እንዲህ ይባላል አለ፡፡ «በሆነ ነገር ሲደነግጡ ‹አቴቴዬን› ገፈፍከው!» ይላሉ። አቴቴ ቃሉ ኦሮምኛ ነው፤ ባህሉም ኦሮሚያ ውስጥ የነበረ ነው፡፡ እነሆ የጎጃም እናቶች እየተጠቀሙበት ነው። የአጼዎቹ የፈረስ ስም «አባ» የሚል ቅጽል አለው። አባ ማለት ኦሮምኛ ነው፤ በኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥ የሚባል ነው፡፡ እነሆ የአጼ ቴዎድሮስ፣ የአጼ ምኒልክ፣ የአጼ ኃይለሥላሴ ... የአጼዎች ሁሉ የፈረስ ስም መነሻው «አባ» ነው፡፡ አባ ታጠቅ፣ አባ ዳኘው፣ አባ ጠቅል... እየተባሉ ይጠራሉ፡፡

ደራሲ በዕውቀቱ ሥዩም ከዓመታት በፊት በጻፈው ጽሑፍ፤ አንድ የብሄር አቀንቃኝ ፖለቲከኛ ከእንቁ መጽሔት ጋር ያደረገውን ቃለ መጠይቅ ይጠቅሳል። ፖለቲከኛው «የኢትዮጵያ ሀገራዊ ማንነት የምንለው የአማራ ባህላዊ ማንነት ነው» ብሏል፡፡ በዕውቀቱ ደግሞ ታሪክን እየጠቀሰ የአንድ ብሄር ብቻ እንዳልሆነ ይሞግታል፡፡ ፖለቲከኞች ለራሳቸው ቁማር የአብሮነት ባህሉን እየጣሉ የሚነጣጥል ዘዴ ነው የሚፈልጉት፡፡ ኢትዮጵያውያን የውጭ ጠላትን ድል ያደረጉት በጋራ እንደሆነ የጠላት ሀገር ሰዎች ሳይቀር መስክረዋል፡፡ አጼ ዮሐንስ አራተኛ ኤርትራ ውስጥ የግብጽ ወራሪን ድል ሲያደርጉ ከግብጽ በኩል ሆኖ ይዋጋ የነበረው አሜሪካዊ ጋዜጠኛ ዊልያም ዴይ አጼ ዮሐንስን ለማገዝ የኢትዮጵያ ብሄሮች ከጫፍ እስከ ጫፍ ይጠራሩ እንደነበር መስክሯል፡፡

በእንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ነው የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ባህልና ወግ የተወራረሰው፡፡ «ከተለያዩ ማዕዘናት የመጡ እነዚህ ኢትዮጵያውን ከዘመቻው የሚያገኙት ድልን ብቻ አልነበረም፡፡ በዘመቻ ወቅት ባህል ይዋዋሳሉ፣ ቃላት ይወራረሳሉ፣ ስንቅ ያዋጣሉ፣ ልምድ ይለዋወጣሉ፡፡ በሂደት ተቃራኒ ከሚመስሉ ልማዶች የነጠረ ኢትዮጵያዊ ባህል እንደ አረቄ ይወጣል፡፡ ይህን በመዋጮ የተገኘ ባህል ‹የአማራ ባህል› ብሎ ማጥበብ የጸና ድጋፍ ያለው አይመስለኝም» ይላል ጸሐፊው በዕውቀቱ ሥዩም፡፡ ከበዕውቀቱ ጽሑፍ አሁንም እንቀንጭብ፡፡

«ኢትዮጵያን የማስተዋወቅ ስራ ሲሠራ አስቀድሞ የሚመጣው የቡና ሥነሥርዓታችን ነው፡፡ አንዲት ጠይም፣ ባለሹርባ ሴት፣ የሐበሻ ቀሚስ ለብሳ ቡና ስትቀዳ የሚያሳይ ምስል በየቦታው ማየት የተለመደ ነው፡፡ ይህ ምስል በሥነ ሥዕል ብቻ የተወሰነ አይደለም። ቢዮንሴ እና ጆን ኬሪ ሀገራችንን በጎበኙበት ሰዓት የቡና ሥነ ሥርዓት ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ይህ ማለት የውጭ እንግዳ የቡና ሥርዓታችንን እንደ ኢትዮጵያዊ መለዮ እንዲመዘግብልን ፈልገናል ማለት ነው።»

ይሄን የቡና ሥነ ሥርዓት ዘርዝረን እንየው። የእያንዳንዱ ብሄር መዋጮ አለበት፡፡ የልጅቷ ሹሩባ የሐማሴን ወይም የተምቤን ባህል ነው፡፡ የሐበሻ ቀሚሷን የሸመነው ሽሮ ሜዳ የሚሠራ የጋሞ ተወላጅ ነው፡፡ ጀበናውን የሠራው የጅማ ሙስሊም ነው፡፡ አቦል፣ ቶና እና በረካ የሚለው የአረብኛ ቃል ነው፡፡ ታዲያ ይሄንን ውህድ ባህል የአማራ ወይም የኦሮሞ ወይም የትግሬ ነው ማለት ፍትሐዊ ነው?

ባህል በጊዜ ብዛት ይለዋወጣል፡፡ የሰው ልጅ ከሥልጣኔ ጋር ራሱን ይለውጣል እንጂ ባለበት አይቆምም፡፡ በዚህም ልውውጥ አንድ አካባቢ የነበረው ወደ ሌላ አካባቢ ይሄዳል፡፡ በዘመን ቅደም ተከተል እንየው ከተባለም፤ ድሮ በባዶ እግሩ ይሄድ ነበርና አሁንም ይሂድ ማለት አይቻልም። ድሮ የወንዝ ውሃ አጎንብሶ ይጠጣ ነበርና አሁንም የወንዝ ወይም የኩሬ ውሃ ይጠጣ ማለት አይቻልም፡፡

ባህል ለምን ተወራረሰ ካልን፤ ድሮ የሰው ልጅ የኑሮ ሥርዓት ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ አስገዳጅ ነበር። እንደ ዛሬው ከቤቱ ቁጭ ብሎ በበይነ መረብ የፈለገውን ማዘዝ አይችልም፤ በቴሌቪዥን መስኮት የፈለገውን ማየት አይችልም፡፡ ያዘዘውን ነገር በቀላሉ ማስመጣት አይችልም። ያለው አማራጭ መሄድና መገበያየት ነበር። ጎንደር ላይ የሚመረት ነገር ወለጋ ውስጥ አይኖርም፤ የወለጋው ጎንደር ውስጥ አይኖርም፡፡ የጅግጅጋው ነዋሪ መቀሌ ድረስ ይሄዳል፤ የመቀሌው ሰው አሶሳ ወይም ጋምቤላ ይሄዳል። በእነዚህ ሁሉ መስተጋብሮች የባህልና የታሪክ ውርርስ ነበር። እንዲህ ነው ኢትዮጵያን የገነቧት።

ከላይ ለዘረዘርናቸው ነገሮች የሰሞኑ የጥምቀት በዓል ምስክራችን ነው፡፡ ጥምቀት የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች በዓል ነው፡፡ የበዓሉን ባህላዊ ይዘት ልብ በሉ! ለዚህ በዓል ብዙ ነገሮች ይገዛሉ፡፡ የበዓሉ ቀን ልብ ብላችሁ ከሆነ ጎዳናው ሁሉ በሻጮች የተጥለቀለቀ ነው፡፡ ያ ሻጭ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ላይሆን ይችላል። እሱማ ልብሱን ለባብሶ ታቦት ያጅባል። የእስልምና ወይም የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዩ ግን የሥራ ልብሱን ለብሶ ለእሱ የጦፈ ገበያ ነው፡፡ አንድ ባለ ሱቅ ሙስሊም የጥምቀት በዓል መምጣት ከኦርቶዶክሱ በላይ ያስቸኩለዋል፡፡ ኦርቶዶክሱ «ምን ልግዛ?» እያለ ሲያስብ፤ ሙስሊሙ ምን ላስመጣ? እያለ ያስባል፡፡ ለጥምቀትና ለገና በዓል የሚገዛዙ ስጦታዎችን ያስመጣቸው የመርካቶ ሙስሊም ነጋዴ ነው። ከዚህም አለፍ ሲል፤ የራሱ የሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓቱ መለያ የሆነውን መስቀል የሚሠራው ሙስሊም የእጅ ጥበበኛ ነው፡፡

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ብሄራዊ ቴአትር በተዘጋጀ አንድ መድረክ ላይ የተናገረው ነገር ትዝ አለኝ፡፡ የብሄር ብሄረሰቦች የአጨፋፈር ባህል እንኳን አቅጣጫውን ተከትሎ ሙሉ ኢትዮጵያን የሚያሳይ ነው፡፡ ከሰሜን ኢትዮጵያ ሲጀምር የትግራይ አጨፋፈር ከአንገት በላይ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው፡፡ የአማራ አካባቢዎች በትከሻ እንቅስቃሴ የሚደረግ ነው፡፡ የኦሮምኛ የባህል አጨፋፈር በአንገትና በወገብ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ወደ ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ስንሄድ ደግሞ በዳሌና በእግር (ለምሳሌ ጉራጌ) የሚደረግ ነው፡፡ በአንድ መድረክ ላይ ሙሉ ኢትዮጵያን ያሳያል ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ባህሎቻችን በስሪት የጋራ እንደ ሆኑ ሁሉ፣ በመንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብትም የሁላችንም ናቸው!!!

# ዓለም አቀፍ

## የየመን ሑቲዎች በአሜሪካ መርከብ ላይ የሚሳኤል ጥቃት አደረሱ

በየመን የሑቲ አማጺያን በአሜሪካ መርከብ ላይ የሚሳኤል ጥቃት ሰነዘሩ። ጥቃቱን ያደረሱት ‘ጂብራልተር ኤግል’ በተሰኘው አቃ ጫኝ ግዙፍ መርከብ ላይ ነው። የመካከለኛው ምሥራቅ የአሜሪካ ማዘዣ ማዕከል ጥቃቱ በየመን ጠረፍ አካባቢ መፈጸሙን አምኖ ነገር ግን የከፋ ጉዳት እንዳልደረሰ አብራርቷል።

የማርሻል አይላንድ አርማን የያዘው ይህ መርከብ ጉዞውን በኤደን ባሕረ ሰላጤ ቀጥሏል። በኢራን ይደገፋሉ የሚባሉት ሑቲዎች በቀይ ባሕር አካባቢ የባሕር ጉዞን ማስተጓጎል የጀመሩት እስራኤል በጋዛ እየፈጸመችው ያለውን ጥቃት በመቃወም ነው። ‘ኤግል በልክ’ የተሰኘው የመርከብ ድርጅት እንዳለው መርከብ ብረት ጭኖ ከኤደን ጠረፍ 160 ኪሜ ምትር ርቀት ላይ እየተጓዘ ነው ጥቃቱ የደረሰበት።

ጥቃቱ ያደረሰው ጉዳት መጠነኛ ስለነበረ መርከቡ ጉዞውን ቀጥሏል ብሏል ኩባንያው። አሜሪካ እንዳለችው ከዚህ የሚሳኤል ጥቃት አንድ ሰዓት ቀደም ብሎ ሌላ ሚሳኤል በሑቲዎች የተተኮሰ ቢሆንም በአሜሪካ ተዋጊ ጄቶች አየር ላይ እንዲመክን ሆኗል። ይህ ሚሳኤል ዒላማ አድርጎ የነበረው በቀይ ባሕር የአሜሪካ ባሕር ኃይልን ነበር።

ሑቲዎች የንግድ መርከቦች ላይ ጥቃት መሰንዘራቸውን እንደሚቀጥሉ ዝተዋል። ሆኖም ጥቃቶቹ በሁሉም የንግድ መርከቦች ሳይሆን ከእስራኤል ጥቅም ጋር የተሳሠሩ ላይ ብቻ እንደሚሆን ተናግረዋል። ሑቲዎች ጥቃቶቹ የሚቀጥሉት እስራኤል በጋዛ በሐማስና በንጹሐን ላይ የምትፈጽመውን ጥቃት እስከቀጠለች ድረስ ነው።

የዩኬ ባሕር ኃይል ይህ ጂብራልተር ኤግል መርከብ ከእስራኤል ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለው አረጋግጫለሁ ብሏል። ሑቲዎች በሰጡት ምላሽ ደግሞ የአሜሪካ ማንኛውም ጥቅም ላይ ጥቃት እንሰነዝራለን ብለዋል። ናሲር አል ዲን የተባሉ የሑቲ ከፍተኛ ባለሥልጣን “የአሜሪካ የሆነ መርከብ ሁሉ ጥቃት ሊሰነዘርበት ይገባል” ብለዋል።

በቀይ ባሕር ሑቲዎች ጥቃት መሰንዘራቸውን ተከትሎ በርካታ ግዙፍ የመርከብ ኩባንያዎች ጉዟቸውን በሌላ አቅጣጫ ለማድረግ ተገደዋል። ይህ ደግሞ በዓለም የንግድ



**በጥቃቱ የከፋ ጉዳት አልደረሰም፤**

መርከብ ሰንሰለት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እየፈጠረ ነው። የትናንትን ወዲያ  የሑቲዎች ጥቃት ተከትሎ የአሜሪካ የትራንስፖርት ሚኒስቴር የአሜሪካ ባንዲራ ያላቸው እና የአሜሪካ ንብረት የሆኑ መርከቦች በቀይ ባሕር የተወሰኑ አካባቢዎች እንዳይጠጉ መክሯል።

ሰኞ ዕለት በዓለም ሁለተኛው ግዙፍ የነዳጅ ኩባንያ የሆነው ኳታር-ኢነርጂ መርከቦች በቀይ ባሕር በኩል እንዳያልፉ ውሳኔ አስተላልፏል። ባለፈው ሳምንት አሜሪካና ዩኬ በሑቲ ቁልፍ ወታደራዊ ይዞታዎች ላይ ከባድ ጥቃት መሰንዘራቸው አይዘነጋም። ጥቃቶቹ የሑቲዎችን አቅም በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያሽመደምደው ይጠበቃል።

ጥቃቶቹ በአየርና ከባሕር የተነሱና በአሜሪካ አጋሮች የጋራ ጥምረት የተሰነዘሩ ሲሆን የሑቲ ሚሳኤሎች እና የአየር መቃወሚያዎች የሚገኙበትን የየመን የጦር ሰፈር ዒላማ ያደረገ ነበር። ጥቃቱን ተከትሎ የዩኬ ጠቅላይ ሚኒስትር ሪሺ ሱናክ 13 የሑቲ የአየር ጥቃት መነሻ ነበሩ የተባሉ የጦር ሥፍራዎች እንዳልነበሩ ሆነው ወድመዋል ብለዋል።

የአሜሪካ ደህንነት በበኩሉ ከአጋሮች ጋር ባለፈው ሳምንት የመን ላይ የተሰነዘረው ጥቃት አንድ ሦስተኛውን የሑቲዎች የጦር መሣሪያን አውድሟል። ዋሺንግተን ኢራንን ከሑቲ የሚሳኤል ጥቃት ጀርባ አለች ስትል ትከሳለች፤ ኢራን ታስተባብላለች። የኢራን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሑሴን አሚር አብዱላሒ ትናንት ሰኞ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ምዕራባውያን በየመን ላይ የሚሰነዝሩትን ጥቃት ማቆም አለባቸው  ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## ሰሜን ኮሪያ ከደቡብ ኮሪያ ጋር የመልሶ መዋሀድ ፖሊሲዋ እንዲቀር አደረገች

ሰሜን ኮሪያ ከደቡብ ኮሪያ ጋር የመልሶ መዋሀድ ፖሊሲዋ እንዲቀር አደረገች። ሰሜን ኮሪያ ከደቡብ ኮሪያ ጋር ለመዋሀድ ያወጣችውን ፖሊሲ ማስቀረቷን አስታውቃለች። የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን በትናንትናው እለት በተዘጋጀው ትልቅ የሕዝብ ስብሰባ ላይ የሀገሪቱ ሕገመንግሥት ደቡብ ኮሪያ “ዋነኛ ጠላት” እንዲል ሆኖ እንዲስተካከል ጥሪ አቅርበዋል።

በሁለቱ ተቀናቃኞች መካከል ጦርነት የሚቀሰቀስ ከሆነ ሕገመንግሥቱ ደቡብ ኮሪያን “መውረርን፣ መግዛትን እና መልሶ መቆጣጠርን” ማካተት እንዳለበት ኪም ተናግረዋል። ኪም ጆንግ ኡን ሰሜን ኮሪያ ጦርነት የመጀመር ፍላጎት የላትም፤ ነገር ግን የማስቀረት ፍላጎትም የላትም ብለዋል።

ኪም በሟች አባታቸው ኪም ጆንግ ሁለተኛ የተገነባውን 'የናሽናል ሪዩኒፊኬሽን' ሐውልትን ጨምሮ የሰሜን-ደቡብ መልሶ መዋሀድን የሚያሳዩ ምልክቶች በሙሉ እንዲፈርሱ ትዕዛዝ ሰጥተዋል ተብሏል። የደቡብ ኮሪያው ፕሬዚዳንት ዩን ሱክ ይኦል በትናንትናው እለት ካቢኔያቸውን ሰብስበው እንደተናገሩት የሰሜን ኮሪያን ድርጊት “ጸረ ሀገር እና ጸረ-ታሪክ” ብለዋል።

ፕሬዚዳንቱ ሰሜን ኮሪያ ደቡብ ኮሪያን የምታጠቃ ከሆነ ከባድ ጥቃት ይገጥማታል ሲሉ አስጠንቅቀዋል። የኮሪያ ባህረ ሰላጤ ወደ ሁለት የተከፈለው ለአስርት ዓመታት የቆየው የጃፓን ቅኝ ግዛት በ1945 ከተጠናቀቀ በኋላ ነበር። ሰሜን ኮሪያ የባለስቲክ ሚሳይል ሙከራዋን በማጠናከሯ ምክንያት በሰሜን ኮሪያ እና በደቡብ ኮሪያ መካከል ያለው ውጥረት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ አይሏል ሲል አል ዐይን ዘግቧል።



**የናሽናል ሪዩኒፊኬሽን ሐውልት**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

## ነፃ ሃሳብ

# የኢትዮጵያ ስኬታማ የዲፕሎማሲ ርምጃዎች

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)

ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚና የብልጽግና ብሎም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ ሂደቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው መልካም የዲፕሎማሲ ግንኙነት ነው፡፡ በዚህም ረገድ ሀገራችን ኢትዮጵያ በበጎ የሚነሳ ስም አላት፡፡ ላለፉት በርካታ ዓመታት በዚህ የዲፕሎማሲ ሂደት ውስጥ ተጉዛ ከራሷ አልፋ ለሌሎች የተረፈችባቸውን የሰላምና የአስታራቂነት ሚና እንዲሁም የነጻነትና የእኩልነት ፋና ወጊነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

የታሪክ ሰነዶቻችን ከጀግንነታችንና ከሉአላዊነት ክብራችን እኩል የሚያነሱት የተግባቦትና የሰላም ወዳድ ጽናታችንን ነው፡፡ እንደሀገር ተሳካልን ብለን አፋችንን ሞልተን በኩራት የምንናገረው ይሄን መቶ ዓመታት የተሻገረ የሰጥቶ መቀበል መርሀችንን ነው፡፡ አፍሪካንም ሆነ መላውን ጥቁር ሕዝብ ከተጫነበት የቅኝ ግዛጥ ቀንበር ነጻ እንዲወጣ በዚህ የዲፕሎማሲ ሂደት ውስጥ አልፈን ስለመሆኑ ነጋሪ የሚያሻው ጉዳይ አይደለም፡፡

ሰሞነኛው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንትም የዚህ ሂደት አንድ አካል ነው፡፡ ‹ከአፍሪካ መዲናነት እስከ ዓለም መድረክ› ” በሚል መሪ ሀሳብ ከጥር 2 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ጥር 24 ድረስ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አዘጋጅነት በሳይንስ ሙዚየም መከፈቱ ይታወቃል፡፡ የተለያዩ ዓላማዎችን ያነገበው አውደ ርዕዩ ሀገራችን የነበራትን ያላትንና የሚኖራትን የዲፕሎማሲ ሂደት በስፋትና በንቃት የቃኘ ነው፡፡ እንደ ሀገር የበለጸግንባቸውና ከራሳችን አልፈን ለሌሎች የተረፍንበትን መልካም ግንኙነት በማስታወስ ያንን ዘመን ከዚህኛው ትውልድ ጋር በማስተሳሰር ላበረቱን ክንዶች ምስጋና የምንቸርበትም ነው፡፡

ሳምንቱን አስመልክቶም ‹ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን› በሚል መሪ ሀሳብ በተካሄደው የፓናል ውይይት የትላንትን የታሪክ ዳራ ከመጥቀስ አንስቶ አሁን እስካለንበትና ነገ እስከምንደርስበት ያለውን የዲፕሎማሲ ሂደት የዳሰሰ ውይይት ተካሄዷል፡፡ በዚህ ውይይት ላይ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ‹የትውልድ፣ የትምህርትና የእውቀት ሽግግርን ለመሙላት በዲፕሎማሲው ዘርፍ ጠንካራ ስራ እየተሰራ› እንደሆነ በንግግራቸው መመስከር ችለዋል፡፡ የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ጉዞ ኢትዮጵያን በመሩ በሁሉም መሪዎች ብርቱ ጥረት የቀጠለ መሆኑን በማስታወስ እንደሀገር በበረታ ዲፕሎማሲ የበረታ ለውጥ እንደሚመጣም አመላክተዋል፡፡

ሌላኛው የዚህ ፓናል ውይይት ተሳታፊ በመሆን በመካከለኛው ዘመን ላይ የነበረውን የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ንቃት በጥናታዊ ጽሁፋቸው ያሳዩት አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ የአፍሪካን የነጻነት እንቅስቃሴ በዲፕሎማሲ በመደገፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረገች እና የአፍሪካ ሕብረትና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ምስረታ ላይም ደማቅ አሻራ እንዳሳረፈች ጠቅሰዋል፡፡ ከሰላምና ከተግባቦት አንጻር ሶስተኛ ወገን ሆኖ በመግባት የአሸማጋይነት ሚናዋንም ያተተው ጥናታዊ ጽሁፉ የኮርያን፣ የላይቤሪያን፣ የሶማሊያን፣ የኩባንና የሩዋንዳን በጎ አሻራ ጠቅሷል፡፡ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴን ጨምሮ አምባሳደር ቆንጅት ስነጊዮርጊስ የዚህ ፓናል ውይይት አንድ አካል ነበሩ፡፡

ለጀመርነውና ውጤት እያመጣንበት ላለው አሁናዊ የዲፕሎማሲ ሂደት መንገድ ጠራጊ አስተሳሰቦችንና ልምዶችን ይዘን ቀጣይ ግንኙነታችን የምናቀላጥፍበት እንደሚሆንም ተስፋ ተችሮታል፡፡ ኢትዮጵያን ገላጭ በሆኑ ልዩ ልዩ ዝግጅቶችና በፓናል ውይይት የታጀበው አውደ ርዕይ ትላንትን ከዛሬ፣ ዛሬን ከነገ በማስተሳሰር በዲፕሎማሲው ዘርፍ ያስመዘገብነውንና እያስመዘገብን ያለውን ወደፊትም የምናስመዘግበውን እድልና ድል ቃኝቷል፣ በመቃኘት ላይም ይገኛል፡፡

በአንድ ገላጭ እውነት ብናስረው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንት የኢትዮጵያ የእውቀት፣ የተግባቦት፣ የሰላም ወዳድነትና፣ የሰጥቶ መቀበል የታሪክ አሻራ ነው፡፡ እንደ አድዋ ሁሉ፣ እንደ ህዳሴ ግድባችን ሁሉ በታሪክ ውስጥ ከፍ ብሎ የሚነሳ የዛኛውና የዚኛው የመጪውም ትውልድ የኩራት ገድል ነው፡፡ ..ዲፕሎማሲ የአንድ ሀገርና ሕዝብ፣ የአንድ መንግስትና አስተዳደር የጥንካሬና የስልጣኔ መመዘኛ ነው፡፡ ዛሬም ይሁን ድሮ በዲፕሎማሲው ረገድ የደከሙ ሀገራት ምንም መፍጠር የማይችሉ እንደሆኑ መረጃ የሚሰጥ እውነታ ነው፡፡

የእኛ ታሪክ ግን እንዲህ አይደለም፡፡ በዛ ዓለም ብዙም ባልነቃችበት ዘመን ስለሀገርና ሕዝብ፣ ስለሰላምና ልማት ባህር ተሻግሮ ከዓለም ሀገራት ጋር ወዳጅነትን መፍጠር አሁን ላለው ትውልድ ኢትዮጵያዊነትን የሚገልጥ፣ ታሪክን የሚያስረዳ፣ ማንነትን የሚያወሳ የታላቅነት መስካሪ ነው፡፡ ዓለም ላይ በቀጣናዊ፣ በአህጉራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ በዚህ ልክ የተጓዘ ሀገርና ሕዝብ የለም ካለም በጣት የሚቆጠር ነው፡፡ ይሄ ማለት ስልጣኔና ዘመናዊነትን ቀድመን ለመጀመራችን አንዱ ምስክር ነው፡፡

የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንት አቅጣጫ ከመተለም ባለፈ ራሳችንን ለተቀረው ዓለም የምንገልጥበት መድረክ ነው፡፡ ወቅትና ጊዜ ተቆርጦለት ቀጣይነት ባለው መልኩ ቢካሄድ ደግሞ ፋይዳው ዘርፈ ብዙ ነው የሚሆነው፡፡ የአፍሪካ የግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤቶች ነን፡፡ በአፍሪካ ቀንድና በአህጉሪቱ በምንም የማይደበዝዝ ደማቅ ስም አለን፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃም ከኢትዮጵያዊነት ጋር አብሮ የሚነሳ የታሪክ፣ የነጻነትና የሉአላዊነት ምኩራብ ነን፡፡ ላሉብን አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ጫናዎች እንደመመከቻ ሆኖ የሚያገለግለን ደግሞ የዳበረና በእውቀትና በልምድ የሚመራ የዲፕሎማሲ ተጽዕኖ ፈጣሪነታችን ነው፡፡

ከአባቶቻችን በወረስነው ሰላም ወዳድ ፖለቲካ፣ ሰላም ወዳድ ጉርብትና እና የአብሮ መልማት መስተጋብር የቀጠናውን ሰላም አስጠብቀን አፍሪካን የዋጀና ዓለምን ያስደነቀ የለውጥና የእድገት ባለቤቶች እንደምንሆን ጅማሬዎቻችን መስካሪዎች ናቸው፡፡ አንድ ሀገር በቀጠናውም ሆኖ ወንዝ ተሻጋሪ በሆነ የእርስ በርስ ጉርብትናዋ ጥሩ ስም ከሌላት ብዙ ነገሮቿ ጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚገቡ ናቸው፡፡ አይደለም ብዙ ነገሮቿ ቀርቶ አንድ ሁለት ጉዳይዋ ጥያቄ የሚያስነሳ ሀገር ራሷን መለስ ብላ እንድታይ የማንቂያ ደውል ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም ዲፕሎማሲ የለውጥ፣ የእድገትና የዘርፈ ብዙ መስኮች መነሻ አውድ ነው፡፡

ተለዋዋጭ በሆነ ዓለም ውስጥ ነን፡፡ አሁን ግዜው የዲፕሎማሲ ነው፡፡ የነበሩንን ገልጠን ያሉንን አጥብቀን ለመጪው አዲስ ሂደት ራሳችንን ማዘጋጀት በአጽንኦት ልናየው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ እንደሀገር የጀመርናቸው ትላልቅ ልማቶች አሉ፡፡ ወደፊትም ልንሰራቸው ያሰብናቸው ጥቂት የሚባሉ አይደሉም፡፡ እኚህ ሕዝባዊ ጸጋዎች ፍሬ አፍርተው ሀገርና ሕዝብ እንዲጠቅሙ መልካም ወዳጅነት የማይናቅ ሚና አለው፡፡

ዲፕሎማሲን በአንድ ሁነኛ ሀገራዊ ልማድ እንግለጸው ብንል..በቡና አጣጭ ጎረቤት ልንወክለው እንችላለን፡፡ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ቡና አጣጫ ጎረቤቶች አሉን፡፡ እነዚያ ጎረቤቶቻችን በሰላሙም በችግሩም ጊዜ አብረውን የቆሙ ናቸው፡፡ ለምንም ነገር አለውለህ የምንባባላቸው ናቸው፡፡ ከነዚህ ጎረቤቶቻችን ውስጥ ከአንዱ ጋር ተኮራርፈን ቡናችንን ለብቻ ስንጠጣና ቡናቸውን ለብቻ ሲጠጡ የሚኖረው ማሕበራዊ ክስረትን መረዳት ይቻላል፡፡ ይሄ ክዋኔ ወደቀጠናዊ ወደ አህጉራዊ እና ወደዓለም አቀፋዊም እውነታ ከፍ ሲል ነባራዊውን ዲፕሎማሲ ይወክላል፡፡ ከኢኮኖሚ፣ ከፖለቲካ፣ ከማሕበራዊ አኳያ ንጻሬውንም መረዳት ይቻላል፡፡

> **በአፍሪካ ቀንድና በአህጉሪቱ በምንም የማይደበዝዝ ደማቅ ስም አለን። በዓለም አቀፍ ደረጃም ከኢትዮጵያዊነት ጋር አብሮ የሚነሳ የታሪክ፣ የነጻነትና የሉአላዊነት ምኩራብ ነን። ላሉብን አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ጫናዎች እንደመመከቻ ሆኖ የሚያገለግለን ደግሞ የዳበረና በእውቀትና በልምድ የሚመራ የዲፕሎማሲ ተጽዕኖ ፈጣሪነታችን ነው**

በሁሉም መስክ ወዳጅነት በሁሉም መስክት ትርፋማነት ነው፡፡ በሁሉም መስክ ጠላትነት በሁሉም መስክ ኪሳራ ነው፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ከሌላው ጋር እንዴት መኖር እንዳለብን የምናውቅ እና መቶ ዓመታትን ያስቆጠረ የጉርብትና ታሪክ ያለን ነን፡፡ ታሪካችን በአብሮ መልማት፣ በአብሮ ማደግና የማንንም ሳንነካ እንዲሁም ማንም የእኛን እንዲነካብን ሳንፈቅድ የሆነ ነው፡፡ ትርጉም ያለውና ውሀ የሚያነሳው ዲፖሎማሲ ደግሞ እንዲህ ያለው ዲፕሎማሲ ነው፡፡ አሁንም በዚህ ጥንተ እውነት ታሪካችን ላይ ሳንገዳገድ በጽናት በመራመድ ኢትዮጵያን ከፍ የማደረጉ ኃላፊነት ተጥሎብናል፡፡

ዲሞክራሲ መቻቻልና መከባበርን የሚጠይቅ ነው፡፡ ያለፉ የዲፕሎማሲ ስርዐቶቻችን ደግሞ በዚህ እውነት ውስጥ ያለፉ ስለመሆናቸው ካገኘነውና ለሌሎች ከሰጠነው ክብርና ሰላም መረዳት እንችላለን፡፡ የራስን ክብርና ሉአላዊነት በማስነካትና የሌሎችን ክብርና ሉአላዊነት በመድፈር ውስጥ የሰጥቶ መቀበል መርህ የለም፡፡ ኢትዮጵያዊነት የተገኘው በፍትህና በእኩልነት ውስጥ በተከፈለ ጽኑ ተጋድሎ ነው፡፡ አንገታችንን ቀና አድርገን የተራመድንባቸው የነጻነትና የወዳጅነት ዳናዎች ማንንም ሳንነካና ማንም እንዲነካን ባለመፍቀድ ውስጥ ነው፡፡

ቀጠናዊ ዲፕሎማሲ ከአፍሪካ አዘልሎ አለምቀፋዊነትን የሚቸር ነው፡፡ ዙሪያችንን ተመልክተን ሁሉንም አይነት የተግባቦት አማራጮች ተጠቅመን ሀገራችንን ነጻ የምናወጣበት፣ ከውጪው ማህበረሰብ ጋር በሁሉም አቀፍ ዘርፍ የምንተባበርበት ጊዜ ላይ ነን፡፡ በዲፕሎማሲ ያሸነፈ ሀገር በምንም አይሸነፍም፡፡ በዚህ ዘመን ላይ የኃይልና የብርታት የለውጥም መለኪያዎች ተደርገው ከተቀመጡት ውስጥ የዲፕሎማሲ ክህሎት አንዱ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተወዳሽ ስም ከማትረፍ ጎን ለጎን ተወዳሽ ስራዎችንም ሰርተናል፡፡

ከሀገራችን የዲፕሎማሲ ፍሬዎች መካከል ታላቁ የሕዳሴ ግድብ፣ የባህር በር፣ የብሪክስ አባልነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እንደ ኢጋድና ተመድ፣ እንደ አፍሪካ ሕብረትና ሊግ ኦፍ ኔሽን የመሳሰሉ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሳረፍናቸው አሻራዎቻችን በድምቀት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በቀጣይም የዚህ ሂደት አንድ አካል የሆኑ ቀጠናዊና ባህር ተሻጋሪ ትልሞች አሉን፡፡ እንደ ኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ሳምንት ዓላማና እቅድ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ክፍተቶቻችንን ሞልተን በአዲስ ኃይል በችግሮቻችን ላይ የምንነሳበት የአዲስ ምዕራፍ ግስጋሴ እንደሚሆን ታምኖበት እየተሰራ ነው፡፡ ካለፈው ተምረን መጪውን ብሩህ የምናደርግበት የስኬታማ ዲፕሎማሲ አቅጣጫዎችቻችንን አበልፅገን የምናስቀጥልበት ነው፡፡

ከእርስ በዕርስ መደጋገፍ ባለፈ ዲፕሎማሲ የዘመናዊነት አንዱ ማሳያ ነው፡፡ አሁን ላይ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ውጤት ማምጣት ብዙም ላይገርም ይችላል ምክንያቱም ጊዜው ለዚህ ነገር ምቹና ተስማሚ ስለሆነ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ከሌላው ሀገርና ሕዝብ ጋር በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የሀሳብ ልውውጥ የጀመሩበት ያ ዘመን እንደዚህኛው ዘመን ለምንም ነገር ምቹ አልነበረም፡፡ በዛ ምቹ ባልሆነ ዘመን ላይ ሁኔታዎችን ምቹ አድርጎ ከዓለም ሀገራት ጋር ወዳጅነትን መፍጠር ቀድሞ መንቃት ከመባል ሌላ ምንም ሊባል አይችልም፡፡

እንዲህ አይነት የሀገርና ሕዝብ፤ የትውልድና የአስተዳደር ንቃቶች አሁን ላለችው ደማቅ ዓለም መሰረት የጣሉ ነበሩ፡፡ ሌላው ከዚህ ጋር አብሮ ሊነሳ የሚችለው ውይይትና ተግባቦትን ያስቀደመ በአብሮ ማደግ ዲፕሎማሲያዊ አረዳድ የዳበረ ኢትዮጵያዊነት ነው፡፡ እኚህ የታሪክ ሁነቶች ዛሬ ላይ ዳብረው በብዙ ዘርፍ ውጤታማ አድርገውናል፡፡ ያላንዳች መጠራጠር ነገም ይቀጥላሉ፡፡

## የንግድ ምልክት ባለቤት ስም ለውጥ ማስታወቂያ

EURAPHARMA. የተሰየመና አድራሻውም 8, avenue Paul Delorme-Zac du Grand Launay, 76120 LE GRAND QUEVILLY, FRANCE የሆነ አድራሻው እንዳለ ሆኖ ስሙን ወደ CFAO HEALTHCARE መለወጡንና ከዚህ በታች ለተመለከተው የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ ግላዊ ባለቤትና ብቸኛ ተጠቃሚ መሆኑ በዚህ ማስታወቂያ ተገልጿል፡፡

FAZZINI

የንግድ ምልክቱ በማመልከቻ ቁጥር FTM/ 8443፣የሚጠቀምበት በምድብ 5፣ 10፣ 11፣ 12 ላይ ሲሆን፤ የንግድ ምልክቱ የምዝገባ ማስረጃም ተሰጥቶታል፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ከባለቤቱ ፍቃድ ውጭ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN- VOL.LXXXIII.No 128 - 8/5/2016 (17/1/2024)

## የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

1. የንግድ ምልክት ባለቤት፡ AL REHAB MODERN FACTORY FOR PERFUMES
አድራሻ፡ Jeddah Industrial City, Phase 4, Jeddah 21431, P.O.Box 1246 , Saudi Arabia
2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/ 7811
3. የጥበቃ ጊዜው፡ 30/8/2023 እስከ 31/8/2030
4. የንግድምልክት፡

Randa

5. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በቀን 27/1/2010 Vol.LXXVII No.027 እና በኢትዮጵያ ሄራልድ በቀን 7/10/2017 Vol.LXXIV No.023 በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው::
6. ይህ የንግድ ምልክት የታደሰ በመሆኑም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፈቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN- VOL.LXXXIII.No 128 - 8/5/2016 (17/1/2024)

## ለሁለተኛ ጊዜ የወጣ የሃራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በአፈ.ከሳሽ አቶ ነጋሽ በላይ እና በአፈ.ተከሳሽ አቶ የሺ በላይ መካከል ስላለው የአፈፃጸም ክስ ጉዳይ ተከሳሹ በተወሰነበት ውሳኔ መሰረት ባለመፈፀሙ ምክንያት የተከሳሹ ንብረት የሆነው በሞላሌ 01 ቀበሌ ልዩ ስሙ ዞን 3 ከተባለው ስፍራ አዋሳኙ በምስራቅ ሰይፈ ጌታነህ በምዕራብ ከበቡሽ ሀ/ወልድ በሰሜን መንገድ በደቡብ በለገ ሸዋይርጋ መካከል የሚገኘው የቦታው ስፋት 100 ካሬ ሜትር የሆነ አምስት ክፍል የመኖሪያ ቤትና ቦታ ሲሆን ይህንን የመኖሪያ ቤትና ቦታ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች ስለሚሸጥ የካቲት 10 ቀን 2016 ዓ/ም ንብረትነቱ በሚገኝበት በሞላሌ 01 ቀበሌ ዞን 3 ከጠዋቱ 5፡00-7፡00 ሰዓት የሃራጅ ጨረታው ይካሄዳል፡፡

ይህንን ቤትና ቦታ በግልፅ ጨረታ መግዛት የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች በቦታው ተገኝቶ ተጫርቶ መግዛት ይችላል፡፡ የጨረታው አሸናፊ አካል የሆነ ያሸነፈበትን ገንዘብ 1/4ኛውን ወዲያውኑ የሚያስይዝ ሲሆን ቀሪውን 3/4ኛውን ደግሞ በ15 ቀን ውስጥ አሟልቶ የሚያቀርብ መሆኑን አውቀው መጫረትና መግዛት የሚፈልጉ በቦታው ተገኝተው መግዛት ይችላሉ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** ፍ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ሃራጁን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ፡-**0919842755 ወይም 0947876750 መደወል ይችላሉ፡፡

**በአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰሜን ሸዋ ዞን የመንዝ ማማ ምድር ወረዳ ፍ/ቤት**

## የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመልካች ስም ፡- እስፖትለስ ጀነራል ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማ<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ 09 የቤት ቁጥር. 552/10 2, አራዳ, አዲስ አበባ /ኢትዮጵያ | | |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር ፡- LTM/15121/2016<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 07/01/2016 E.C. | | |
| 3 | ምልክት፡ | 4 | የምልክቱ መግለጫ፡- የምስል |
| | | 5 | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁር እና ነጭ |
| | | 6 | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡- |
| | | 7 | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 37 እና 45 |
| 8 | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | የፅዳት አገልግሎት (ምድብ 37) እና የጥበቃ አገልግሎት (ምድብ 45) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፈቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN- VOL.LXXXIII.No 128 - 8/5/2016 (17/1/2024)

ENGAGE NOW AFRICA

## የጨረታ ማስታወቂያ

ኢንጌጅ ናው አፍሪካ (Engage Now Africa) የተባለ አለም አቀፍ የበጎ አድራጎት ድርጅት እ.ኤ.አ. ከJan. 01/2023-Dec. 31/2023 በIPSAS የተሰራውን ዓመታዊ የሂሳብ ክንውኑን የመንግስት ፈቃድ ባላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች ማስመርመር ይፈልጋል፡፡

በመሆኑም የዘመኑን ግብር የከፈለ እና የሂሳብ ምርመራ ፈቃድ ያለው ማንኛውም ድርጅት ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በመያዝ ቢሾፍቱ /ደብረዘይት/ ከተማ በሚገኘው የድርጅቱ ቢሮ በግምባር በመቅረብ ወይም ከዚህ በታች በተገለፀው አድራሻ በመላክ መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**ፖ.ሳ.ቁ. 1607**
**ስልክ 0118489100**
**0913491023**
**ቢሾፍቱ**

## ኢንጌጅ ናው አፍሪካ

# ኦሮሚያ ክልል

በከሳሽ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና በተከሳሽ አቶ አሌክስ ልዑልሰግድ መካከል ባለው የፍትሐብሄር የካሣ ገንዘብ ክርክር በተመለከተ መከሰስዎን አውቀው ለ13/5/2016 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ለሆነ ቀጠሮ መልስዎን በፅሁፍ አዘጋጅተው እንዲቀርቡ፣ የማይቀርቡ ከሆነ መልስ የመስጠት መብትዎ ታልፎ ክርክሩ የሚቀጥል እና በሌሉበት ጉዳዩ የሚታይ መሆኑን የሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**የሰሜን ሸዋ ኦሮሚያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

# ሐረሪ ክልል

በአቶ ዋሊ ዳውድ ዴቅኔ ስም ተመዝግቦ ስለሚገኝ የሰሌዳ ቁጥር 03-00646 ሐረ የሆነ ተሽከርካሪ የፊት ታርጋ ጠፋብኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ በማንኛውም መልኩ ይዤዋለሁ የሚል ቢኖር ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት እንዲያመለከቱ እያስታወቅን ባያመለከቱ ምትክ ታርጋ የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የሐረሪ ሕ/ክ/መንግሥት የትራንስፖርት ጽ/ቤት**

# ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል

ለአብርሃም አዲሴ
ባሉበት
በከሳሽ የሀዲያ ዞን አቃቤ ህግ እና በተከሳሽ በእርሶ መካከል ስላለው ተራ የሆነ ሰው መግደል ወንጀል ክስ ጉዳይ መከሰስዎን አውቀው ለ15/05/2016 ዓ/ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 2:30 ሰዓት የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት እንዲቀርቡ ሆኖ ባይቀርቡ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን ጭምር የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል

**በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት**
**የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

አቶ ተገኝ ታደሰ ገብሬ
ባሉበት
በከሳሽ የሀዲያ ዞን አቃቤ ህግ እና ተከሳሽ ተገኝ ታደሰ ገብሬ መካከል ስላለው በህገ ወጥ መንገድ ሰውን ድንበር ማሻገር ወንጀል ክስ ክርክር ጉዳይ መከሰስዎን አውቀው ለ23/05/2016 ዓ/ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት አንድ እንዲቀርቡ ሆኖ ባይቀርቡ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን ጭምር የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት**
**የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

# አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም አብደላ እብራሂም የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A28309 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር VNKKV12370A043002 ሞዴል SCP10L-CHMRGKW የሞተር ቁጥር 1SZ-U044484 የሊብሬ ቁጥር 384766 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ4/5/2016 አመልክተዋል፡፡
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረበ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በከሣሽ ወ/ሮ ፌቨን አበበ ግርማ እና በተከሣሽ አቶ ሚካኤል መስፍን አለሙ መካከል ስላለው የቤተሰብ ክስ ጉዳይ ተከሣሽ በ21/05/2016 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ በ4፡30 ሰዓት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ 3ኛ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች፡- እነ አቶ ሰሎሞን ወ/ፃዲቅ እና በተከሳሽ/ተጠሪ፡- አቶ ምንተስኖት መለሰ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ውርስ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ ተጠሪ በ16/05/2016 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ አቶ ሚስባህ ፋሪስ ኡስማን እና
በተከሳሾች 1ኛ አቶ ምስባ ፋሪስ ኡስማን
2ኛ አቶ ገ/መስቀል ተወልደ ወ/ገብርኤል
3ኛ አቶ ተፈሪ መኮንን ተሰማ
ባለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች በ21/05/2016 ዓ.ም. በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 3ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

የባለንብረት ስም አስር አለቃ አበበች ጉልማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-14053 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAMJP34G4Y7P02599 ሞዴል NPR66 የሞተር ቁጥር 4HF1-332903 የሊብሬ ቁጥር 434700 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ3/5/2016 አመልክተዋል፡፡
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች/የፍ/ባለመብት ህዳሴ ትራንስፖርት እና ንግድ ኢ.ማ እና በተከሣሽ/ተጠሪ የፍ/ባለዕዳ 1ኛ አቶ አበበ ዳላ /ጣ/ገብ/ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 3ኛ ንግድ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ16/05/2016 ዓ.ም. በ4፡30 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡና ክስ ለመስማት ለ22/05/2016 ዓ.ም. በ8፡30 ሰዓት ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**
**የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ አቶ ደሳለኝ አሰፋ እና በተከሳሽ ወ/ሮ ህይወት ትዕዛዙ መካከል ስላለው የቤተሰብ ክስ ጉዳይ ተከሳሽ ወ/ሮ ህይወት ትዕዛዙ በ15/05/2016 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ እንገልጻለን፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ አቶ ኢዮብ ሰለሞን እና በተከሳሽ አቶ ፍቃዱ ማሞ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ አቶ ፍቃዱ ማሞ ለ21/05/2016 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አራዳ ምድብ 1ኛ ልዩ ልዩ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡


**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# በንጉሱ ከልብ የተወደደው ቢትወደድ

አስመረት ብስራት



በአፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት በተለይ ከአድዋ ድል በኋላ የአገሪቷን የውጭ ጉዳይ እንዲያስፋፉ ባለሙሉ ሥልጣን ሆነው የተሾሙ ሰው ነበሩ። ንጉሠ ነገሥቱ ከሹመቱ በተጨማሪ የቢትወደድነት ማዕረግ የተሰጣቸው በንጉሱ የተወደዱ ሰውም ነበሩ። በዚህ ኃላፊነት ሥራቸው ንጉሠ ነገሥቱን ወክለው የውጭ አደራዳሪዎችን ያነጋግራሉ፣ ከኃያላን መንግሥታትም ጋር ይጻጻፋሉ። ከአማርኛ ሌላ በጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጣልያንኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሠለጠኑ ስለነበሩ ለዚህ ሥራ ብቃት የነበራቸው ሰው ነበር።

ቢትወደድ አልፍሬድ ኢልግ ይባላሉ። በዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ኑሮውን ኢትዮጵያ ውስጥ የመሠረቱ፤ የስዊትዘርላንድ ዜጋ ነበሩ። ኢልግ በምሕንድስና ሙያው ባቡር እና የቧንቧ ውሀ ለአገራችን ካስተዋወቋቸው ብዙ ዘመናዊ የሥልጣኔ መስመሮች ሁለቱ ሲሆኑ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ታላቅ ታማኝነትን በማፍራቱ የዘውድ አማካሪ እና የአገሪቱን የውጭ ጉዳይ እስከ መምራትም የበቁ ሰው ነበሩ።

ቢትወደድ ኢልግ በዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ብዙ ሚና ከተጫወቱ አውሮፓውያን መካከል በሀገሪቱ ባሳለፏቸው ሃያ ሰባት ዓመታት እና ባስቀመጧቸው የልማት አሻራዎቹ የታሪክ ሥፍራው በጣም የጎላ ነበር።

ኢልግ በ ስዊትዘርላንድ፣ ፍራውንፌልድ በሚባል ከ ዙሪክ ከተማ በሰሜን-ምሥራቅ አቅጣጫ በሚገኝ ሥፍራ በ መጋቢት ወር በ1846 ዓ.ም ተወልዶ በስድሳ ሁለት ዓመቱ የገና ዕለት ( ታሕሣሥ 29 ቀን) ፲፱፻፰ 1908 ዓ.ም ዙሪክ ላይ በልብ ሕመም ምክንያት አረፈ።

### ኢልግና ኢትዮጵያ

ታዋቂው የታሪክ ምሁር ሪቻርድ ፓንክኸርስት ዳግማዊ ምኒልክ ገና በልጅነታቸው የ ዓፄ ተዎድሮስ እስረኛ በነበሩ ጊዜ ቴዎድሮስ አጠገባቸው የነበሩትን አውሮፓዊ ወንጌላውያን መድፍና መሣሪያዎች እንዲሠሩላቸው ማግባባታቸውን ልብ አድርገው ነበርና የሸዋ ንጉሥ ሲሆኑ በ ኤደን ላይ የነበረ አንድ የስዊትዘርላንድ ዜጋ ነጋዴ ምሕንድስና የሚያውቁ አውሮፓውያን ባለሙያዎችን እንዲፈልግላቸው ጠይቀውት ነበር ይላል።

ኢልግ እና ሁለት የአገሩ ሰዎች በ ፲፰፻፸ 1870 ዓ.ም አካባቢ ጉዞዋቸውን ወደ ኢትዮጵያ አምርተው ሸዋ ሲገቡ ንጉሥ ምኒልክ መጫሚያ እንዲሠራላቸው ያዙትና ሠርቶ ባበረከተላቸውም መጫሚያ እጅግ እንደተደሰቱ ይነገራል። በሌላ ዘገባ ደግሞ ንጉሡ ኢልግን ጠመንጃ እንዲሠራላቸው አዘዙት።

ኢልግ ጠመንጃ ለመሥራት ሙያ እንደሌላቸውና ከውጭ የሚመጣ መሣሪያ እሱ ከሚሠራው እጅግ የላቀ እንደሚሆን ቢያስረዱም፤ ምኒልክ ኃሳባቸውን የማይለውጡ ሆኑ። ከዛም እንደተጠየቁት የሙከራውን ውጤት ሲያሳይዋቸው ንጉሡ ተደስተው ይሄንኑ ጠመንጃ በግምጃ ቤታቸው የክብር ቦታ ሰጡት ብለው አዘዙ። ከዛ በኋላ በምሕንድስና ሥራ በደሞዝተኝነት ቀጥረውት በየወሩ ሰባት ወይም ስምንት ፓውንድ በጠገራ ብር ይከፈላቸው እንደነበር ፓንክኸርስት ዘግቧል።

### ኢልግ የሰሩት ድልድይ

ኢልግ ከሠሯቸው አንዱ አዋሽ ወንዝ ላይ የቆመው ድልድይ ነው። ስለዚህ ድልድይ ሥራ ኢልግ ሲጽፉ፤ የመጀመሪያው የድልድይ ሥራ እንደነበረና የድልድዩ ቋሚዎች በሰው ሸክም አሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ተጉዘው እንደመጡ ይተርክና ሥራውን በሐሩር እና በዶፍ እንዲሁም በማታ የዱር አራዊትን በመቋቋም እራሳቸው ድንጋይ እየጠረቡ፣ ምስማር፣ ችንካር እና ብሎን እያቀለጡ እየቀጠቀጡ እንደሠሩት ይናገራሉ።

### ባቡር በኢትዮጵያ

ምኒልክ በሸዋ ንጉሥ ከሆኑ በኋላ ሐዲድ አዘርግተው ባቡር ለማስገባት አሰቡ። ይህም ሀሳባቸው እንዲፈቀድላቸው የበላያቸውን ንጉሠ ነገሥቱን አጤ ዮሐንስን ፈቃድ ጠየቁ። በአጤ ዮሐንስ አካባቢ የነበሩ መኳንንቶች መክረው ምኒልክ ከግዛታቸው ከሸዋ ውጭ ሐዲድ ለመዘርጋት እንደማይችሉ ተነገራቸው። በሳቸው መቸኮልና መጓጓት ምክንያት አልፍሬድ ኢልግ በሥራና በሀሳብ ተጠምደው እንደነበር ወዲያውም ለ ጃንሆይ ምኒልክ የሞዴል ባቡር ተጎታች ጋሪዎችን እየጎተቱ በሐዲድ ላይ ሲሄድ የሚያሳይ ሠርቶ ሲያሳያቸው በጣም እንደተደሰቱ ጳውሎስ ኞኞ "አጤ ምኒልክ" በተባለው መጽሐፋቸው ዘግበዋል።

ከ ዓፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ ምኒልክ የንጉሠ ነግሥትነትን ዘውድ በ ጥቅምት ወር ጭነው ወዲያው በ ኅዳር ወር ላይ የምድር ባቡርን ሥራ አንቀሳቅሰዋል። ለዚህም ኢልግ ከማንኛውም ኩባንያ ጋር ተዋውለው ሐዲዱን ለማሠራት የሚችልበትን ፈቃድና የሚዋዋልበትን የውል ዓይነት መጋቢት ፲፩ ቀን 1886 ፲፰፻፹፮ ዓ.ም አስጽፈው በማህተማቸው አትመው ሰጡት። ኢልግም ፓሪስ ከተማ ላይ ቢሮ ከፍተው ለሥራው የሚያስፈልገውን መዋእለ ነዋይ፤ ሥራውን የሚኮናተሩ ድርጅቶችን እና ሌላም ጥናቶችን ማቀናበር ጀመሩ።

የዚህ የምድር ባቡር መሥመር ከ ጂቡቲ ወደብ ተነስቶ አዲስ አበባ ድረስ 784 ፯፻፹፬ ኪሎ ሜትር ሲሆን ሥራው በ 1890፲፰፻፺ ዓ.ም ተጀምሮ ከሀያ ዓመታት በኋላ በ 1910 ዓ.ም ተገባደደ። መቸም የኃሳቡ ጠንሳሽ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክም ሆኑ ሕልማቸውን ዕውን በማድረግ ብዙ አስተዋጽዖ ያስመዘገበው ኢልግም ፍጻሜውን ባያዩትም በኢትዮጵያ የምድር ባቡርን ስናስብ የእነዚህ የሁለቱ ሰዎች ትዝታ በታሪክ ተመዝግቦ ይኖራል።

### ፖስታ

ዳግማዊ ምኒልክ በመንግሥታቸው ስርዓትን ለማስገባት፤ ኢትዮጵያ ከ አውሮፓ "ክርስቲያን ሕዝብ" ጋር እንዲለማመድ እና በዋናነት ግን በ1885 ፲፰፻፹፭ ዓ.ም ለ አድዋ ጦርነት መንስዔ የሆነውን የውጫሌ ውል ካፈረሱ በኋላ እንደልባቸው ከውጭው ዓለም ጋር ያለ ኢጣልያ ጣልቃ ገብነት መገናኛ መንገድ አስበው የፖስታ ስርዓትን ሲመሠርቱ በጊዜው የፖስታ ማኅበር ዋና መሥሪያ ቤት በ ስዊስ ከተማ በርን ላይ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ የፖስታ ድርጅት ከተቋቋመ በኋላ ወደ ውጭ አገር ከጻፏቸው ደብዳቤዎች አንዱ ሐምሌ 13 ቀን 1887 ዓ/ም ኢልግ ወደ አገሩ ሄዶ በነበረበት ጊዜ ለሱ የጻፉት ይጠቀሳል። የኢልግ መልስ ምን እንደነበር ባናውቅም፣ ምኒልክ ግን የቱን ያህል ናፍቀውት እንደነበር እንገነዘባለን።

### የእንጦጦው ቤተ መንግሥት ግንባታ

የእንጦጦ ቤተ መንግሥት የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ዋና ከተማቸውን ከ አንኮበር ወደ እንጦጦ ሲያዛውሩ መጀመሪያ የሠፈሩት በድንኳን ነበር። ወዲያ መሐንዲሳቸው አልፍሬድ ኢልግ አዲስ ቤተ መንግሥት እንዲያሠራላቸው በሰጡት ትዕዛዝ መሠረት፣ አሁን ድረስ ቆሞ በቤተ ቅርሳ ቅርስነት የሚያገለግለውን ሕንጻ አሠራላቸው።

ቤተ መንግሥቱ ከአንኮበሩ ቤተ መንግሥት ያነሰ እና በዚያ ጊዜ የነበሩትን ቤተ መንግሥቶች ያህል ስፋት የለውም በሚል በጊዜው ነቀፋ ተሰንዝሮበት ነበር። ሆኖም ምኒልክ የ ንጉሠ ነገሥቱን ሥልጣን እስከጨበጡ ጊዜ ድረስ ተገልግለውበታል። አንዳንዴም ወደ ሰሜን ሲጓዙ ወይም እንጦጦ ማርያምን ሊሳለሙ ሲሄዱ ያርፉበት እንደነበር ይታወቃል። እሳቸውም ከሞቱ በኋላ እቴጌ ጣይቱ እስከ ዕድሜያቸው መጨረሻ ድረስ በግዞት ኖረውበታል።

አዲስ አበባም የሚገኘው "ታላቁ" ወይም "የምኒልክ ቤተ መንግሥት" በ 1890 ፲፰፻፺ ዓ/ም ላይ መታነጽ ሲጀምር ኢልግ በምሕንድስናው ሥራ ላይ ብዙ ተሳትፎ እንደነበረው ተጽፏል። በጊዜው ከተማዋን ትጎበኝ የነበረች፣ ወይዘሮ ፒስ የምትባል እንግሊዛዊት "(በቤተ መንግሥቱ) ብዙ (የስዊስ ባሕር ምስል እና የዊሊያም ቴል ጸሎት ቤት) ስዊሳዊ ተጽእኖዎች እንደተገነዘበች መፃፏን ሪቻርድ ፓንክኸርስት በፅሁፋቸው ገልፀውታል።

### ንፁህ የቧንቧ ውሃ ለቤተመንግስቱ

ደራሲ ጳውሎስ ኞኞ ስለዚህ ሥራ በሰፊው ሲያጫውቱን ሥራው በ1886 ፲፰፻፹፮ ዓ/ም እንደተጀመረና ለቧንቧ መግዣ ሰባት ሺ ማርያ ጠሬዛ ብር እንደሰጡ፤ ውሃው ከእንጦጦ ኪዳነ ምኅረት ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ተጠልፎ ከቤተ መንግሥቱ እንደገባ ይነግሩናል። የቤተ መንግሥቱ የቧንቧ ውሃ ከተገጠመ በኋላ ምኒልክ አዲስ አበባ ከተማ በሙሉ እንዲዳረስ የውሃ ቧንቧ አስገዝተው ቧንቧው ከ ጂቡቲ እስከ ድሬዳዋ በምድር ባቡር፣ እስከ አዲስ አበባ ደግሞ በሰው ሸክም እንዲመጣ አዘዙ። ሆኖም እሳቸው ያሠሩት የቧንቧ ውሃ እምብዛም ሳይስፋፋ እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ ቆየ።

ሆኖም በዘመኑ የምኒልክ እንግዳ ሆኖ ኢትዮጵያን የጎበኘው አሜሪካዊው ዊሊያም ኤሊስ በምኒልክ አዳራሽ "ለኔ ክብር በተዘጋጀ ሰባት ሺ ሰዎች በተጋበዙበት ግብር ላይ፣ ጠጅ የሚባለውን መጠጥ በግብር ቤቱ ዙሪያውን በተገጠመ ቧንቧ የፈለገው ሰው እየተነሳ ከቧንቧው ይቀዳል።" ሲል ተናግሯል።

አጼ ሚኒሊክ በቢትወደድ ኢልግ የተነሡት ፎቶግራፍ ዳግማዊ ምኒልክ ኢልግን የውጭ ዜጋም ቢሆን እንኳ ያከብሩትና ያምኑትም ነበር። ትውልድ አገሩ ስዊስ የቅኝ ግዛት ምኞት የሌላትና ትንሽ፣ የ ባሕር ወደብ የለሽ እና ከሌላ አውሮፓዊ ኃያል መንግሥታት ጋር ያልተሻረከች መሆኗም የኢልግን ታማኙት ሳያጠናክረው አልቀረም።

ኢልግም በበኩሉ "እንደ አባቴ እወዳቸዋለሁ" ያላቸውን ምኒልክን ለሀያ ዓመታት በታማኝነት አገልግሏል። ኢልግ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ወደ ትግራይ እና ዝዋይ የመሳሰሉ ቦታዎች ተጉዟል። እንዲሁም ወደ ጣልያን አገር ተጉዞ ከሚንስትሮቻቸው ጋር ከተወያየ በኋላ ሲመለስ ኢጣልያ ኢትዮጵያ ን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ሀሳብ እንዳላት ዳግማዊ ምኒልክን አስጠንቅቋቸዋል።

ከጦርነቱም በኋላ የ አድዋ ድልም ያስከተለውን የድርድር (diplomacy) መስፋፋት እንዲያስተዳድር እና የአገሪቷን የውጭ ጉዳይ እንዲይስፋፋ ባለሙሉ ሥልጣን አደረጉት። ንጉሠ ነገሥቱ ኢልግን ሲሾሙት አብረውም የ ቢትወደድን ማዕረግ ሰጡት። በዚህ ኃላፊነት ሥራው ንጉሠ ነገሥቱን ወክሎ የውጭ አደራዳሪዎችን ያነጋግራል፣ ከኃያላን መንግሥታትም ጋር ይጻጻፋል። ሰውዬው ከ አማርኛ ሌላ በጀርመንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ጣልያንኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሠለጠነ ስለነበር ለዚህ ሥራ ብቃት የነበረው ሰው ነበር።

ከንጉሠ ነገሥቱም ሌላ ከብዙ ኢትዮጵያውያን መሳፍንት፣ መኳንንትና ሹማምንትም ጋር ይጻጻፍ እንደነበር ተዘግቧል። ከነኚህም መሃል እቴጌ ጣይቱ፣ የ ጎጃም ንጉሥ ተክለሃይማኖት፣ የ ሐረርጌው ገዥ ልዑል ራስ መኮንን፣ የ ጅማው አባ ጅፋር እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ አቡነ ማቴዎስ ይገኙበታል።

ከ አድዋ ድል በኋላ በ ኢጣልያ እና ኢትዮጵያ መሃል ጥቅምት ፲፮ 16 ቀን 1889 ፲፰፻፹፱ የተፈረመውን የዕርቅ ውል፤ ከ ብሪታንያ እና ከ ፈረንሳይ መንግሥታት ጋር በ መጋቢት ወር የተፈረሙትን ውሎች

እንዲሁም ከጀርመን መንግሥት እና ከኦቶማን ግዛት መንግሥት ጋር የተፈረሙ ውሎችን በማዘጋጀትም ሆነ እስከ ማዋዋል ድረስ ኢልግ ሙሉ ተሳትፎ እንደነበረው ታሪክ ይዘግባል።

ወደ መጨረሻው ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱም ጤናቸው እየደከመ መጣ። በቤተ መንግሥቱም እሱን የሚመቀኙት ሰዎች በዙ። ከሁሉም ግን የካቲት ወር 1897 ፲፰፻፺፯ ዓ/ም የ ጀርመን ልዑካንን የመራው ፍሬድሪክ ሮሰን የተባለው ጀርመናዊ በ ኢትዮጵያ መንግሥት እና በ ጀርመን መንግሥት መሃል ብዙ ውሎችን ከተፈራረመ በኋላ በቤተ መንግሥቱ የኢልግ ተሰሚነት እየመነመነ ሄዶ በ ፲፱፻፪ ዓ/ም ሥራውን ለቆ ወደትውልድ አገሩ ተመለሰ።

ወደአገሩ ከተመለሰ በኋላ በእሪ በከንቱ ሠፈር ያለው መኖሪያ ቤቱ የመጀመሪያው ዘመናዊ ትምህርት ቤት (የአሁኑ ዳግማዊ ምኒልክ) በ 1901 ፲፱፻፩ ዓ/ም ተከፈተበት። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ትምህርት ቤቱ አሁን አራት ኪሎ ወዳለበት ሥፍራ ተዛወረ። አልፍሬድ ኢልግም በተወለደ በስድሳ ሁለት ዓመቱ የ ገና ዕለት

(ታሕሣሥ ፳፱ 29 ቀን) 1908 ዓ/ም ዙሪክ ላይ በልብ ሕመም ምክንያት አረፈ።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ረቡዕ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# በቤት ውስጥ ቱር ውድድር ዓለም ኢትዮጵያውያኑን አትሌቶች ይጠብቃል

ብርሃን ፈይሳ

ይህ ወቅት በአትሌቲክስ ፖርት የቤት ውስጥ ውድድሮች በስፋት የሚከናወንበት መሆኑ ይታወቃል። በየካቲት ወር አጋማሽ ላይ ስፖርቱን በሚመራው አካል የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና የሚካሄድ መሆኑን ተከትሎ በመላው ዓለም በሚገኙ በርካታ ከተሞች ውስጥ የቤት ውስጥ ቱር ውድድሮች ይከናወናሉ። በአውሮፓ፣ እስያ እና ሰሜን አሜሪካ አህጉራት በሚገኙ 20 ከተሞች ውስጥ ከ50 በላይ የሚሆኑ ውድድሮች የሚደረጉ ሲሆን፤ እነርሱም በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ፣ የብር፣ የነሃስ እንዲሁም ውድድር የሚል ደረጃ ተሰጥቷቸዋል።

የፈረንጆቹ አዲሱ ዓመት ከመግባቱ ከሁለት ቀናት በፊት የተጀመረው ይህ የቱር ውድድር የዓለም ቻምፒዮናው ከመካሄዱ 6 ቀናት በፊት የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ በሜዳ ተግባራት እንዲሁም ከ60 ሜትር እስከ 5ሺ ሜትር ባሉት ርቀቶች አትሌቶችን ያፎካክራሉ። እያንዳንዱ የቱር ውድድር የገንዘብ ሽልማት ሲያስገኝ፤ አትሌቶች በሚኖራቸው ተሳትፎ የሚያስመዘግቡት ነጥብ ተደምሮ በዓለም አቀፉ ቻምፒዮና በቀጥታ ሃገራቸውን ወክለው የሚሳተፉበትን እድል ሊያስገኝላቸው ይችላል። ከዚህም ባለፈ ከፍተኛ ነጥብ የሚያገኙ አትሌቶች በመጨረሻው ውድድር 10ሺ የአሜሪካ ዶላር ጉርሻ በማግኘትም በውድድር ዓመቱ የመጀመሪያው በሆነው ዓለም አቀፍ ቻምፒዮና የሚፎካከሩም ይሆናል። በእንግሊዟ ግላስኮ አዘጋጅነት የሚደረገው ይህ የቤት ውስጥ ቻምፒዮናም ዘንድሮ ለ19ኛ ጊዜ ይደረጋል።

በዓለም አትሌቲክስ ደረጃ የተሰጣቸው የቱር ውድድሮች በተከታታይ እየተካሄዱ ሲሆን፤ ታዋቂ አትሌቶች በተለይ የሚካፈሉባቸው የወርቅ ደረጃ ያላቸው ውድድሮች ግን ከቀናት በኋላ ነው የሚጀምሩት። የእስያዋ ካዛኪስታን በዋና ከተማዋ አስታና የምታካሂደው ውድድር ቀዳሚው ሲሆን፤ በውድድሩ ዝናን ያተረፉ አትሌቶች መሳተፋቸውን አረጋግጠዋል። ነገር ግን ከእነዚህ መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያዊቷ የመካከለኛና ረጅም ርቀት አትሌት ጉዳፍ ጸጋይ ተሳትፎዋን እንደሰረዘች ታውቋል። የቤት ውስጥ ቻምፒዮናን ጨምሮ በኦሊምፒክ፣ በዓለም ቻምፒዮና፣ በዳይመንድ ሊግ እንዲሁም በሌሎች ውድድሮች ኢትዮጵያን ያስጠራችው የ5ሺ ሜትር ንግስቷ፤ የውድድር ዓመቱን በካዛኪስታን ትጀምራለች በሚል ቢጠበቅም ለቀናት ማራዘሟ ነው የተረጋገጠው። ነገር ግን በ1ሺ 500 ሜትር ርቀት እንደምትሳተፍ አስቀድማ ያሳወቀችው



በቤት ውስጥ ውድድሮች በውጤታማነት ከሚጠቀሱ አትሌቶች መካከል አንዷ አትሌት ጉዳፍ ጸጋይ፣

አትሌት ሂሩት መሸሻ እንዲሁም በ3ሺ ሜትር የሚሮጠው አትሌት አሊ አብዲልማና ሃሳባቸውን ሳይቀይሩ የሚሮጡ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ናቸው።

ጠንካራዋ አትሌት ጉዳፍ ጸጋዬ በበኩሏ የወርቅ ደረጃ ባለውና ቦስተን ላይ በሚካሄደው ኒው ባላንስ ግራንድ ፕሪክስ የተለመደ አስደማሚ ብቃቷን ለማሳየት ተዘጋጅታለች። ባለፈው የውድድር ዓመት አስደናቂ ጊዜ ያሳለፈችው አትሌቷ ከቡዳፔስቱ ስኬታማ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና መልስ በዳይመንድ ሊግ የ5ሺ ሜትር ክብረወሰን መስበሯ የሚታወስ ነው። በዚህም አትሌቷ የዓለም ምርጥ አትሌት እጩ መሆኗ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ጉዳፍ በቤት ውስጥ ውድድርም በ1ሺ500 ሜትር ስኬታማ ስትሆን፤ እአአ 2016 ፖርትላንድ ላይ ሃገሯን በመወከል የነሃስ ሜዳሊያ ባለቤት ነበረች። ኢትዮጵያ ከዓለም አንደኛ ደረጃን ይዛ ባጠናቀቀችበትና ከሁለት ዓመት በፊት ቤልግሬድ ላይ በተደረገው ቻምፒዮና ደግሞ በዚሁ ርቀት የወርቅ ሜዳሊያ ማጥለቅ ችላለች። በመሆኑም አትሌቷ ካለችበት ወቅታዊ አቋም እና ካላት ልምድ አንጻር በቱር ውድድሩ ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገብ ለቻምፒዮናው ቀጥታ መሳተፍ የምትችልበትን እድል ታገኛለች የሚለው ግምት በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ አይሏል።

በሌላ በኩል በዚህ መድረክ እጅግ ተጠባቂና ውድድሩንም ከሚያደምቁ አትሌቶች መካከል አንዱ ኢትዮጵያዊው ለሜቻ ግርማ ነው። በዓለም ቻምፒዮና የሶስት ጊዜ እንዲሁም በኦሊምፒክ አንድ ጊዜ የብር ሜዳሊያ ያገኘው ወጣቱ አትሌት ኢትዮጵያን በ3ሺ ሜትር መሰናክል ካስጠሩ ጥቂት አትሌቶች መካከል አንዱ ነው። ቤልግሬድ ላይ በነበረው ቻምፒዮናም በተመሳሳይ የብር ሜዳሊያውን መውሰድ ችሎ ነበር። ይህ አትሌት ባለፈው ዓመት ሌቪን ላይ በተደረገው የቤት ውስጥ ቱር ውድድር ርቀቱን 7:23.81፣ ከቤት ውጪ ደግሞ 7:52.11 በሆነ ሰዓት በመሸፈን ሁለቱንም ክብረወሰኖች ከእጁ ማስገባቱም አይዘነጋም። ይህም ውድድሩን አጓጊ የሚያደርገው ሲሆን፤ ተፎካካሪዎቹን በአሳማኝ ብቃት በመርታት ግላስኮ ላይ ኢትዮጵያን የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት ያደርጋታል የሚለውም ተጠባቂ ነው።

በዚህ ውድድር ከሚካፈሉና አሸናፊ ይሆናሉ በሚል ተስፋ ከተጣለባቸው አትሌቶች መካከል ኢትዮጵያዊቷ ወጣት አትሌት መዲና ኢሳ ትጠቀሳለች። የዓለም ከ20 ዓመት በታች የ5ሺ ሜትር ክብረወሰን ባለቤቷ ወደ አዋቂነት የሚያሸጋግራትን ብቃት እንደምታሳይም ተገምቷል።